




# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ


## የ2016 በጀት ዓመት

## የተደገፈ በጀት

## (ጥራዝ I በጀት ማጠቃለያ)

ግንቦት 29/2015


ጠቅላላ ወጪ /በቢሊዮን ብር/
የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ 14.00 , 2%
መደበኛ 370.14 , 46%
ክልል ድጋፍ 214.07 , 27%
ካፒታል 203.44 , 25%


ጠቅላላ ገቢ /በቢሊዮን ብር/
የአገር ውስጥ ብድር 242.04 30%
የአገር ውስጥ ገቢ 479.49 60%
የውጭ አገር ብድር 39.01 5%
የውጭ አገር እርዳታ 41.12 5%

# ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1
2. የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም (2012-2014) ........ 2
3. ያለፉት ዓመታት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም (2012-2014) ........ 8
   3.1 የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም (2012-2014) ........ 8
      3.1.1 የመንግስት ገቢ አፈጻጸም ........ 8
      3.1.2 የመንግስት ወጪ አፈጻጸም ........ 9
      3.1.3 የበጀት ጉድለት እና የመንግስት ዕዳ ሁኔታ ........ 10
      3.1.4 የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ........ 11
4. የ2015 በጀት አፈጻጸም ዕይታ ........ 14
   4.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ........ 14
   4.2 የ2015 በጀት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም ........ 15
5. የ2016 በጀት ዓመት ገቢ፣ ወጪና የወጪ አሸፋፈን ........ 16
   5.1 ኢኮኖሚያዊና ፊሲካል ታሳቢዎች ........ 17
      5.1.1 ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ........ 17
      5.1.2 የፊሲካል ፖሊሲ ታሳቢዎች ........ 19
   5.2 የፌዴራል መንግሥት የገቢ ታሳቢዎች ........ 20
   5.3 የፌዴራል መንግስት ወጪ ........ 23
      5.3.1 የፌደራል መንግስት መደበኛ ወጪ ........ 24
      5.3.2 የፌደራል መንግስት ካፒታል ወጪ ........ 24
      5.3.3 የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ ........ 25
      5.3.4 የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ........ 25
6. የ2016 ፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና ድጋፍ ........ 26
   6.1. የ2016 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ዋና ዋና ታሳቢዎች ........ 26
      6.1.1 ጠቅላላ ታሳቢዎች ........ 26
      6.1.2 የመደበኛ ወጪ ታሳቢዎች ........ 28
      6.1.3 የካፒታል ወጪ ታሳቢዎች ........ 29
   6.2. ጠቅላላ በጀት ........ 30
      6.2.1 የመደበኛ ወጪ ........ 32
      6.2.2 የካፒታል ወጪ ........ 37
      6.2.3. ከፌዴራል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ........ 42
7. የወጪ አሸፋፈን ........ 44

# 1 መግቢያ

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዓለማችን በተከሰቱ ቀውሶች ምክንያት የበርካታ ሀገራት ኢኮኖሚ ዕድገት በእጅጉ የተዳከመ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሀገራችንም ከነዚህ አለም አቀፍ ተግዳሮቶች በተጨማሪ ባጋጠሟት ዘርፈ-ብዙ ውስጣዊ ተግዳሮቶች የተነሳ የተያዙት ኢኮኖሚውን የማረጋጋት እና የኢኮኖሚ ዕድገቱን የማስቀጠል ውጥኖች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፈጠሩ አልቀረም፡፡ ምንም እንኳን መንግስት እነዚህን ተግዳሮቶች ለማለዘብ የተለያዩ እርምጃዎችን የወሰደ ቢሆንም፣ ከተግዳሮቶቹ ግዝፈት እና መደራረብ የተነሳ ችግሮቹን ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ከዚህም በተያያዘ መንግስት የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያን በመተግበር በእነዚህ ተግዳሮቶች ምክንያት ሊከሰት ይችል የነበረውን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ለመቀነስ የተቻለ ቢሆንም፣ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ ሀገራችን በገጠሟት ተደራራቢ ተግዳሮቶች ምክንያት በሪፎርሙ በመጀመሪያ አመታት ላይ የተስተዋሉ አመርቂ ውጤቶችን ማስቀጠል ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ምንም እንኳን ባለፉት ዓመታት የተወሰዱ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ተፈጥረው የነበሩትን መጠነ ሰፊ ችግሮች ኢኮኖሚው ተቋቁሞ እንዲሄድ ቢያስችሉትም፣ እንደ የዋጋ ግሽበት፣ ከፍተኛ የብድር ጫና፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ስራ አጥነት ያሉ ችግሮች ትልቅ ተግዳሮቶች ሆነው መቀጠላቸው አልቀረም፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በሩሲያና ዩክሬን መካከል እየተካሄደ የለው ጦርነት፣ በሀገራችን አንዳንድ አካባቢዎች ተከስቶ የነበረው አለመረጋጋት እና ከነዚህ ጋር ተያይዘው የመጡ ችግሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ሆኖም ይህ ሰነድ በሚዘጋጅበት ወቅት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲካሄድ የነበረው ጦርነት ተቋጭቶ የሰላም ስምምነት በመፈረም የሰላም አየር እየነፈሰ እና የሌሎች ተግዳሮቶችም ተጽኖ እየቀነሰ ባለበት ሁኔታ በመሆኑ በቀጣይ በጀት ዓመት መልካም የበጀት አፈጻጸም እንደሚኖር ይገመታል፡፡

በተጨማሪም የ2016 በጀት የገጠመንን ስር የሰደደ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ከግምት ውስጥ በማስገባት እና በአሁኑ ወቅት በተጓዳኝ በመዘጋጀት ላይ ካለው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለት ጋር ተጣጥሞ የተዘጋጀ ነው፡፡

ይህ ሰነድ በቅድሚያ ያለፉት ሶስት ዓመታት የአጠቃላይ ኢኮኖሚና የፊሲካል ፖሊሲ አፈፃፀምን በአጭሩ በመዳሰስ ይጀምራል፡፡ በመቀጠልም የኢኮኖሚና የፊሲካል ፖሊሲ አቅጣጫዎች የዳሰሰ ሲሆን፣ ቀጥሎም የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ የዘጠኝ ወራት የኢኮኖሚና ፊሲካል አፈጻጸም በአጭሩ ከቀረበ በኂላ በመጨረሻም የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ዝርዝር የገቢ፣ የወጪና የወጪ አሸፋፈን ዕቅድ ከትንታኔ ጋር ቀርቧል፡፡

## 2 የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም (2012-2014)

**ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተለያዩ ውጣ ውረዶችን እያለፈ የመጣ መሆኑ ይታወቃል።** መንግስት ባለፉት አራት አመታት ተግባራዊ ያደረጋቸው መጠነ ሰፊ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ኢኮኖሚው የገጠሙትን ተግዳሮቶችንና ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም እንዲችል (resilience building) ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ አይካድም። ምንም እንኳን የኢኮኖሚ ማሻሻያዎቹ በሪፎርሙ መጀመሪያ አመታት አመርቂ ውጤቶችን ማሳየት ጀምረው የነበረ ቢሆንም፤ አገሪቷ በገጠሟት የተለያዩ ፈተናዎች ምክንያት የተገኙትን አወንታዊ ለውጦች በሚፈለገው መጠን ማስቀጠል ሳይቻል ቀርቷል። ሀገራችን ከገጠሟት ተግዳሮቶች መካከል በአገሪቱ የሰሜኑ ክፍል የተከሰተው ግጭት፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ የሩሲያ-ዩክሬን ግጭት፣ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ ወዘተ. ይጠቀሳሉ። መንግስት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ባይጀምር ኖሮ በእነዚህ ሁሉ ፈተናዎች ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ቀውስ መገመት አዳጋች አይሆንም።

**በሌላ በኩል ባለፉት ሦስት አመታት ሀገሪቱ ላጋጠማት ዘርፈ-ብዙ ፈተናዎች እልባት ከመስጠት ጎን ለጎን ወሳኝ የሆኑ በዘላቂነት አይበገሬ የኢኮኖሚ ልማት ለመገንባት መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ተግባራት ተከናውነዋል።** ከነዚህም መካከል የአረንጓዴ አሻራ፣ የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር፣ እንዲሁም የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና ስርዓተ ምግብን ማሻሻል እንደዋነኛ ዓላማ በመውሰድ በመተግበር ላይ ነው። በሌላም በኩል ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሲሰራበት የነበረው ምርትና ምርታማነት ውጤት አፍርቶ፣ የስንዴ ምርትን ከራስ አልፎ ወደ ውጭ መላክ የተጀመረ ሲሆን ይህም የውጭ ምንዛሬ ከማመንጨት በተጨማሪ በትጋት እና ቁርጠኝነት ከሰራን እንደሃገር ለውጥ ማምጣት የምንችል መሆናችንን ማሳያ እንደሚሆን ይጠበቃል። እነዚህ ጥረቶች በአጠቃላይ ምርት እና ምርታማነትን እና የስራ ዕድል ፈጠራን የሚያጎለብት የኢኮኖሚ ሽግግር አጀንዳን ለማፋጠን ዕድል ይሰጣሉ ተብሎ ይታመናል።

**ባለፉት ሶስት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ዕድገት ማሳየቱን ቀጥሏል።** ባለፉት ዓመታት የበርካታ የዓለም ሀገራት ኢኮኖሚ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። በሌላ በኩል ሀገራችን ከየትኛውም ጊዜ ይልቅ ዘርፈ-ብዙ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎችን የተጋፈጠች ቢሆንም ቀደም ሲል ተግባራዊ በተደረጉ መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እንዲሁም መንግስት ኢኮኖሚውን ለመታደግ በየጊዜው እየተወሰዱ ባሉ እርምጃዎች የተከሰቱትን ተጽእኖዎችና ተግዳሮቶች ለመቋቋም አስችሎታል፡

በ2014 በጀት ዓመት በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፍ ከሚመዘገበው ፈጣን ዕድገት የሚመነጭ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ8.7 በመቶ እንደሚያድግ ግብ ተቀምጦ ነበር። ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ ኢኮኖሚው ያጋጠሙት ፈታኝ ሁኔታዎችን በማለፍ በ6.4 በመቶ ማደግ ችሏል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር ሲታይ ያነሰ ቢሆንም በሀገሪቱ ተከስተው ከነበሩ አለመረጋጋት፣ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ካጋጠመው ጦርነት እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ ከተከሰተው የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት አንጻር የተሻለ አፈጻጸም መሆኑን ያሳያል። ይህም ከ2012-2014 ባሉት ጊዜያት በአማካይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ 6.3 በመቶ አድጓል። ይህም በሀገሪቱ ከተከሰቱ በርካታ አሉታዊ ችግሮች አንጻር የተመዘገበው ዕድገት በአስቸጋሪ ወቅትም ቢሆንም በመንግስት በተካሄዱ ጥረቶች የተገኘ አስደማሚ ውጤት ነው። ይህ የዕድገት መጠን ከሰሐራ በታች ያሉ አገራት ካደጉበት የ3 በመቶ ዕድገት አንጻር ሲታይ በእጥፍ የበለጠ ነው። በሌላ በኩል ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ (current market prices) በ2012 በጀት አመት ከነበረበት ብር 3.4 ትሪሊዮን በ2014 በጀት አመት ወደ ብር 6.2 ትሪሊዮን ከፍ ብሏል። እንዲሁም የጠቅላላ ኢንቨስትመንት አፈጻጸም የመቀዛቀዝ አዝማሚያ በማሳየት በ2011 በጀት አመት ከነበረው የ35.3 በመቶ ድርሻ እየቀነሰ በመምጣት በ2014 በጀት አመት ወደ 28 በመቶ ዝቅ ብሏል። ከፍላጎት አንጻር የተመዘገበው የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በአመዛኙ ከፍጆታ የመነጨ መሆኑን ያሳያል። ይህም መረጃው እንደሚያሳየው አጠቃላይ ፍጆታ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር ድርሻው በ2012 በጀት አመት 79.2 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2014 ወደ 84.7 በመቶ ከፍ ብሏል። በአጠቃላይ አማካይ የዜጎች የነፍስ-ወከፍ ገቢ በ2014 በጀት ዓመት ወደ 1,218 የአሜሪካ ዶላር ከፍ ማለቱን የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ ያመለክታል።

ባለፉት ሶስት ዓመታት የበርካታ የዓለም ሀገራት ኢኮኖሚ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰ ሲሆን፣ ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል ሀገራት ከዜሮ በታች ዕድገት አስተናግደዋል። ከዚህ አንጻር በሀገራችን ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ የተደረጉ መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የተከሰቱትን ተጽእኖዎችና ተግዳሮቶች ለመቋቋም እንዲችል አቅም በመፈጠሩ ነው።

ባለፉትና በያዝነው በጀት ዓመታት የዋጋ ንረት ባለ ሁለት አሀዝ ዕድገት እያሳየ በመሆኑ የኢኮኖሚው ከፍተኛ ፈተና ሆኖ ቀጥሏል። በኢኮኖሚ ማሻሻያው ትግበራ ውጤት ያልታየበት የዋጋ ንረት ጉዳይ ሲሆን፣ በግንቦት 2014 የዋጋ ንረቱ የ37.2 በመቶ ጣሪያ ከነካ በኃላ የተወሰነ መሻሻል በማሳየት በያዝነው የ2015 በጀት አመት መጋቢት ወር 34.2 በመቶ ደርሷል። ከላይ ከተጠቀሱ ተግዳሮቶች ጋር በተያያዘ፣ ባለፉት ሶስት አመታት ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋነኛ ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል። ምንም እንኳን የአገር በቀሉ

ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታን በመፍጠር ለኢኮኖሚ ዕድገት አጋዥ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠ ቢሆንም እየተስተዋለ የሚገኘውን የዋጋ ንረት ሁኔታ አሁንም ትልቅ ፈተና እንደሆነ ቀጥሏል።

ይህ የዋጋ ንረት በምግብ እና ምግብ ነክ ባልሆኑ ዕቃዎች የዋጋ መጨመር ምክንያት የመጣ ቢሆንም በአብዛኛው በምግብ ዋጋ ግሽበት ምክንያት የመጣ መሆኑና ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ የታየው መሻሻል የምግብ ነክ ሸቀጦች የዋጋ ንረት መሻሻል ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑን ላይ ማየት ይቻላል።

በአጠቃላይ በያዝነው በጀት አመት ለተስተዋለው የዋጋ ንረት የተለያዩ መንስኤዎች ሊኖሩት ቢችሉም እንደ አንድ ዋና ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው ከሩስያ-ዩክሬን ግጭት ተያይዞ የመጣው የአለም አቀፍ የሸቀጦች እና የነዳጅ ዘይት ዋጋ መናር ነው። ሌላው በኢኮኖሚ ውስጥ የነበረው ፈጣን የገንዘብ አቅርቦት ዕድገት ከነበረው ፈጣን የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን መቀነስ ጋር ተዳምሮ ለዋጋ ንረቱ ተጨማሪ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ከዚህም በተጨማሪ በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በሰሜኑ ክፍል ከነበሩት ያለመረጋጋት ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የምርት እና የአቅርቦት መስተጓጎሎች ለዋጋ ንረቱ የራሳቸውን አስተዋፅኦ እንዳበረከቱ እሙን ነው።

መንግስት የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር በእጁ ዉስጥ ያሉ መሳሪያዎችን እየተጠቀመ ቢሆንም ከላይ በተጠቀሱት ተግዳሮቶች ምክንያት እና የአንዳንዶቹ እርምጃዎች ውጤት ረጅም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የዋጋ ንረቱን በቶሎ በቁጥጥር ውስጥ ማስገባት ሳይቻል ቆይቷል። ይሁን እንጂ የአብዛኛዎቹ ተግዳሮቶች ተጽእኖ እየቀነሰ በመምጣቱ እና እንደ አንድ መፍትሄ የተወሰደው የሀገሪቷን የግብርና ምርት እና ምርታማነት መጨመር ስራ ፍሬያማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቅርብ ጊዜያት ውስጥ መታየት የጀመረው መሻሻል እንደሚቀጥል ከግምት ውስጥ ማስገባት ይቻላል። የዋጋ ንረቱን አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ፣ በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ያለውን የሰላም ሁኔታ ማሻሻልን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ የፊሲካልና የገንዘብ ፖሊሲዎችን መተግበር፣ እንዲሁም የአቅርቦት፣ የንግድ ሥርዓትና ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ በጥናት የተለዩ የተቀናጁ እርምጃዎችን መውሰድን የሚጠይቅ መሆኑ እሙን ነው።

ከፖለቲካ ለውጡ ጀምሮ የውጭ ዘርፉን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም፣ ከኮቪድ ወረርሽኝና ከጦርነቱ ጋር ተያይዘው የተከሰቱ ተግዳሮቶች በዘርፉ አመርቂ ውጤቶች እንዳይመዘገቡ ማድረጋቸው ሌላው

የታየው የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ገጽታ ነው፡፡ ደካማ አፈጻጸም ይስተዋልበት የነበረውን የወጪ ንግድ ለማሻሻል የውጭ ምንዛሬ ማስተካከያ ፖሊሲ ተግባራዊ ከማድረግ ጀምሮ ዘርፉን ተብትበው የያዙትን የተለያዩ መዋቅራዊ ችግሮች ለመፍታት እርምጃዎች በመወሰድ ላይ የነበሩ ቢሆንም፣ ጥረቶቹ የተሟላ ፍሬ ሳያጎመሩ በሀገሪቱ የሚገኙ የማምረቻ ተቋማት ተጨማሪ ተግዳሮቶችን በማስተናገዳቸው ምርቶቻቸውን በሚፈለገው ደረጃ አምርተው ለውጭ ገበያ እንዳያቀርቡ ከኮቪድ ወረርሽኝ ጀምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የሚነሱ የጸጥታ ችግሮች ፋብሪካዎቹ በሙሉ አቅማቸው እንዳይሰሩ በማድረጋቸው የሚጠበቀውን ያህል ምርት ወደ ውጭ ልኮ ከሁሉም የምርት ዓይነቶች ሊገኝ የሚገባውን ያህል የኤክስፖርት ገቢ ማግኘት አልተቻለም፡፡

በተለይ መንግስት በኢኮኖሚው ማሻሻያው ያስቀመጣቸውን ግቦች ለማሳካት የውጭ ምንዛሬ ክምችት ማሳደግ ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ከህልውና ዘመቻ ጋር በተያያዘ ከልማት አጋሮች ይገኛል ተብሎ የታሰበው ፋይናንስ በሚፈለገው ልክ ባለመምጣቱ እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ዕቃዎች ፍላጎት በመጨመሩ ምክንያት የውጭ ምንዛሬ ክምችት በሚፈለገው መጠን ለመያዝ አዳጋች አድርጎታል፡፡ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ መንግስት እጅግ ወሳኝ ባልሆኑ የገቢ ዕቃዎችን (non-essential import) በሚመለከት ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የውጭ ምንዛሬ የማይፈቀድላቸው የገቢ ዕቃዎችን ዝርዝር ይፋ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል ባለፉት ሁለት ዓመታት የወጪ ዕቃዎች ንግድ አፈጻጸም ይበል የሚያሰኝ እምርታ ያሳየ ቢሆንም ለኢኮኖሚ ልማቱ አስፈላጊ የሆነውን የውጭ ምንዛሬ ከማቅረብ እንዲሁም በኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ከተቀመጠው ግብ አኳያ አፈጻጸሙ አሁንም ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በእርግጥ በአንዳንድ የምርት ዓይነቶች (ለአብነት በ2013 በወርቅና ማዕድን፣ በ2014 ደግሞ በቡና ምርት) የዓለም ገበያ ዋጋ መሻሻል በማሳየቱ የኤክስፖርት ገቢያችን አፈጻጸም እንዳያሽቆለቁል ማድረግ ከመቻሉም በላይ በሌሎች ምርቶች የታጣውን ገቢ ማካካስ ተችሏል፡፡

በተለይም ተጨማሪ እሴት ፈጥሮና ምርቶችን በማስፋት ከኤክስፖርት የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ የተደረገው ጥረት ብዙም ርቀት አልተጓዘም፡፡ ይህም የውጭ ምንዛሬ ክምችት ችግራችንን በአስተማማኝ ምንጭ ላይ ለማድረግ የተያዘውን ተስፋ አፈጻጸሙ ከሚጠበቀው በታች እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የኤክስፖርት ገቢያችን በ2013 በጀት ዓመት የ20.7 በመቶ ዕድገት በማሳየት ከዘርፉ 3.5 ቢሊዮን ዶላር የተገኘ ሲሆን፣ በ2014

በጀት ዓመት የኤክስፖርት ገቢያችን የ16.4 በመቶ ዕድገት በማሳየት ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘርፉ 4.1 ቢሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል።

በአጠቃላይ የንግድ ሚዛን መዛባትን ለማስተካከል የወጪ ንግዱን መሰረት ማስፋትና በግብርና ሸቀጦች ላይ ያለውን ጥገኝነት መቀነስ አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ፤ ለነዳጅ እና የፍጆታ እቃዎች ሀገሪቷ የምታወጣው የውጭ ምንዛሬ የሚቀንስበት መንገድ ላይ መስራት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ነዳጅ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ማዋልና የፍጆታ እቃዎችን በሀገር ውስጥ ምርት በመጨመር መተካት ላይ መስራት፤ ለዚህም ምቹ የፖሊሲ ከባቢ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ማስመር ያስፈልጋል። በዚህ አግባብ የሀገሪቷን የውጭ ምንዛሬ ክምችት መጨመር ካልተቻለ አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ከባድ ያደርገዋል።

በሀገር በቀሉ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ በርካታ ማሻሻያዎች ተግባራዊ የተደረገበት የገንዘብ ፓሊሲ አፈጻጸም ባለፉት ሶስት አመታት ያስመዘገበው የ24.7 በመቶ አመታዊ አማካኝ ዕድገት በአስር አመቱ ዘላቂ ዕቅድ ከተቀመጠው የ21 በመቶ አማካኝ የዕድገት ኢላማ አንጻር ከፍተኛ ነበር ማለት ይቻላል። በተለይም በ2014 በጀት ዓመት የገንዘብ አቅርቦት የ27.2 በመቶ ዕድገት ማሳየትና 1.7 ትሪሊዮን ብር መድረስ ለተስተዋለው የዋጋ ንረት እንደ አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ከዋጋ ንረት ጋር የቅርብ ትስስር ያለው ከባንክ ውጭ ያለ ገንዘብ (Currency Outside Banks) በ2013 በጀት ዓመት ከነበረው የ22.5 በመቶ የዕድገት ምጣኔ ጭማሪ በማሳየት በ29.8 በመቶ ማደጉ በበጀት ዓመቱ ለተስተዋለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት የራሱን አሉታዊ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ መገመት ይቻላል።

የገንዘብ ፓሊሲን ከማጠናከር አንፃር የትሬዠሪ ቢል ገበያ እንዲጠናከር በማድረግ ውጤታማ የገንዘብ ሥርጭት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ማድረግ የተቻለ ከመሆኑም ባሻገር የመንግሥትን የበጀት ጉድለት ለዋጋ ንረት በማይዳርጉ የአሸፋፈን (financing) ሥርዓቶች ለመሸፈን ታስቦ አብዛኛውን የመንግስት ግምጃ ቤት ሰነድ በመሸጥ ከሚገኝ ብድር በመጠቀም መሸፈን ተችሏል። የአገር በቀሉ የኢኮኖሚ ሪፎርም ተግባራዊ ከሆነ ወዲህ መንግሥት ከሀገር ውስጥ የሚበደረውን ብድር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲገደብ በማድረግ በተለይም ከብሔራዊ ባንክ የሚወስደውን ቀጥተኛ ብድር በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ እንዲሁም ቀስ በቀስ ሙሉ ለሙሉ ለማቆም ግብ ተይዞ ነበር። ሆኖም በተለይም በሰሜኑ ክፍል የተከሰተውን ግጭት ተከትሉ ከልማት አጋሮች በበጀት ድጋፍ መልክ የሚገኘው ብድርና እርዳታ ሙሉ በሙሉ በመቋረጡ እና ለህልውና ዘመቻ የሚያስፈልገው የፋይናንስ ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ መንግስት ከሀገር

ውስጥ የሚወሰደው ብድር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር አስገድዶታል። በተለይም ለመንግስት በጀት ጉድለት መሸፈኛ ከብሔራዊ ባንክ በቀጥታ የተወሰደው ብድር ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል። ምክንያቱም በግጭቱ ምክንያት ለተፈናቀሉ ዜጎች ለእለት ደራሽ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋም እንዲሁም የወደሙ መሰረተ-ልማቶችችን ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚያስፈልገው የወጪ ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ የአገር ውስጥ ብድር ፍላጎት እንዲጨምር አድርጓል። ይህም ሆኖ ብድር አወሳሰድን በሚመለከት መንግስት የተከተለው ፖሊሲ በተቻለ መጠን የዋጋ ንረትን በማያባብስ መልኩ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በዚህም ምክንያት የአገር ውስጥ ብድርን በአብዛኛው በትሬዠሪ ቢል ለመሸፈን ተሞክሯል።

ከገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያ አንጻር ሌላው የታየው አወንታዊ ለውጥ ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠው የብድር ድርሻ ከፍተኛ ዕድገት እንዲያሳይ መደረጉ ነው። ይህም የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ ከተወሰደው አንዱ እርምጃ ነው። በሌላ በኩል ባለፉት ዓመታት የተቀማጭ ገንዘብ (Deposit mobilization) ከፍተኛ ዕድገት ያሳየ ሲሆን ከባንክ ውጭ ያለው የገንዘብ ዝውውር (Currency outside banks) መጠነኛ ጭማሪ ያሳየ ከመሆኑ ባሻገር በአብዛኛው ዕድገቱ ጤናማ የሚባል ነው።

እንዲሁም የፋይናንስ ዘርፉን ለማሳደግ ከተወሰዱ ማሻሻያዎች አንዱና ዋነኛው የካፒታል ገበያን ለማቋቋም የተወሰደው እርምጃ ሲሆን፣ የፀደቀውን የህግ ማዕቀፍ ሥራ ላይ ለማዋልና ተቋሙን ለማደራጀት እንዲሁም አቅምን ለመገንባት የሚያስችሉ በርካታ ተግባራቶች ተከናውነዋል።

# 3 ያለፉት ዓመታት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም (2012-2014)

## 3.1 የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም (2012-2014)

### 3.1.1 የመንግስት ገቢ አፈጻጸም

ምንም እንኳን ባለፉት ሶስት አመታት የነበረው የመንግስት ገቢ አሰባሰብ የተወሰነ እድገት ቢያሳይም፤ በወቅቱ ከነበረው የዋጋ ንረት አንጻር (in real terms) አፈጻጸሙ ደካማ እንደነበር መገንዘብ ያስፈልጋል። የመንግስት ገቢ አሰባሰብ አፈጻጸም በየዓመቱ በበጀት ከሚጸድቀው የታክስ ገቢ ዕቅድ አንጻርም ከሚጠበቀው በታች የነበረ ሲሆን፤ ከአቻ ሀገሮች አንጻር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበረው የታክስ-GDP ጥመርታም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመሻሻል ይልቅ እያሽቆለቆለ ሄዷል። ከመንግስት ገቢ አንጻር የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋና ግብ ከኢኮኖሚ ዕድገቱ አንጻር የታክስ ገቢ አሰባሰብን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሻሻል ዕድገት እንዲያሳይ ማድረግ ነበር። በዚህ ረገድ በ2011 በጀት ዓመት መጀመሪያ ግማሽ ዓመት ተስፋ ሰጪ የታክስ አሰባሰብ ታይቶ የነበረ ቢሆንም በቀጣይ ዓመታት ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰት ጋር ተያይዞ በተፈጠረው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መዳከም ምክንያት የተጠበቀው ውጤት ሳይገኝ ቀርቷል። ከዚያ በኂላ ባሉት ዓመታትም ከህግ ማስከበር ዘመቻው ጋር ተያይዞ በገቢ ረገድ የተጠበቀዉን ያህል አፋጻጸም ሊታይ አልቻለም።

**ሠንጠረዥ 1፣ ከ2012-2014 በጀት ዓመታት ሀገራዊ የመንግስት ገቢ አፈፃፀም**

በቢሊዮን ብር

| | 2012 | 2013 | 2014 | አማካይ የገቢ ድርሻ | አማካይ ዓመታዊ ዕድገት |
|---|---|---|---|---|---|
| **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢና ዕርዳታ** | 395.0 | 449.7 | 525.7 | 100.0 | 15.1 |
| **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ** | 354.3 | 415.4 | 499.0 | 92.3 | 17.1 |
| **የታክስ ገቢ** | 311.5 | 361.7 | 436.8 | 80.8 | 17.6 |
| *ቀጥታ ታክስ* | 132.2 | 170.8 | 206.8 | 36.9 | 21.4 |
| *የሀገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች* | 78.9 | 84.2 | 98.6 | 19.2 | 8.4 |
| የገቢ ዕቃዎች ታክሶች | 100.4 | 106.6 | 131.3 | 24.7 | 21.2 |
| **ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች** | 42.8 | 53.7 | 62.3 | 11.5 | 13.8 |
| **የውጭ ዕርዳታ** | 40.7 | 34.3 | 26.7 | 7.7 | -5.6 |
| ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ (በመቶኛ) | | | | | |
| **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢና ዕርዳታ** | 11.7 | 10.4 | 8.5 | | 10.2 |
| **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ** | 10.5 | 9.6 | 8.1 | | 9.4 |
| **የታክስ ገቢ** | 9.2 | 8.3 | 7.1 | | 8.2 |
| **ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች** | 1.3 | 1.2 | 1.0 | | 1.2 |
| **የውጭ ዕርዳታ** | 1.2 | 0.8 | 0.4 | | 0.8 |

ባለፉት ሶስት ዓመታት (ከ2012-2014) ጠቅላላ የመንግስት ገቢ 15.1 በመቶ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የታክስ ገቢ ዓመታዊ ዕድገት 17.6 በመቶ ነበር፡፡ የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ የመንግስት ገቢ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ (በአማካይ 80.8 በመቶ) ሲሆን፣ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2010 ከነበረበት 10.7 በመቶ እያሽቆለቆለ በመምጣት በ2014 በጀት ዓመት 7.1 በመቶ ደርሷል፡፡ በነዚህ ዓመታት በታክስ ፖሊሲና በታክስ አስተዳደር በርካታ ማሻሻያዎች የተደረጉ ቢሆንም፣ ኢኮኖሚው ከገጠመው ተግዳሮት ጋር ተያይዞ የማሻሻያዎቹ ውጤቶች ሊታዩ አልቻሉም፡፡ የውጭ ዕርዳታ አሰባሰብ በ2011 እና በ2012 ከፍተኛ ዕድገት ቢያሳይም፣ የሰሜኑን ጦርነት መጀመር ተከትሎ የልማት አጋሮች ለ2013 እና 2014 በጀት መሸፈኛ ለመስጠት ቃል የገቡትን ቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አቁመዋል፡፡ ይሄም በመሆኑ በነዚህ የበጀት ዓመታት የነበረው የውጭ ዕርዳታ አሰባሰብ በቅደም ተከተል የ15.7 እና 22.2 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል፡፡

### 3.1.2 የመንግስት ወጪ አፈጻጸም

ባለፉት ሦስት ዓመታት ጠቅላላ የመንግስት ወጪ በየዓመቱ የ24 በመቶ አማካይ ዕድገት ያሳየ ሲሆን፣ የመደበኛና የካፒታል ወጪዎች በቅደም ተከተል የ30 በመቶና የ15.2 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት አስመዝግበዋል፡፡ በተወሰነ ደረጃ ይህ የወጪ ዕድገት ከዋጋ ዕድገት ጋር የተያያዘ እንደሆነም መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህ የመንግስት ወጪ የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት ለተያዙ የመሠረተ ልማትና የማህበራዊ ልማት ፕሮጀክቶች ማካሄጃ ትኩረት እንዲያደርግ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ከአጠቃላይ ወጪ ውስጥ በሦስቱ አመታት በአማካይ 55.6 በመቶው ለትምህርት፣ ለመንገድ መሠረተ ልማት፣ ለጤና፣ ለግብርናና ውሀ ወጪ የተደረገ ነው፡፡ ከአጠቃላይ ወጪ ውስጥም በሦስቱ አመታት በአማካይ 38.6 በመቶ የሚሆነው ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማካሄጃ የወጣ ወጪ ነው፡፡

ሆኖም የኮቪድ ወረርሽኝ እና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተከሰተው ጦርነት ከተጀመረ በኋላ ወረርሽኙን ለመከላከል እና በጦርነቱና በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ለተጎዱ ወገኖቻችን ለሚያስፈልገው የሰብዓዊ ድጋፍ የሚያስፈልገው የወጪ ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል፡፡ የሚሰበሰበው የመንግስት ገቢ እነዚህን ተጨማሪ የወጪ ፍላጎቶች ለማስተናገድ የሚበቃ ባለመሆኑ፤ በተወሰነ ደረጃ የወጪ ማሸጋሸግ /expenditure reprioritization/ ማድረግ በማስፈለጉ በመንግስት የወጪ ፖሊሲ አቅጣጫ አፈጻጸም ላይ ጫና መፈጠሩ አልቀረም፡፡

**ሠንጠረዥ 2፣ ሀገራዊ የመንግስት ወጪ አፈጻጸም**

በቢሊዮን ብር

| የወጪ ዓይነት | 2012 | 2013 | 2014 | አማካይ ድርሻ | አማካይ ዓመታዊ ዕድገት |
|---|---|---|---|---|---|
| **ጠቅላላ ወጪ** | 488.2 | 599 | 785.4 | 100 | 24.0 |
| መደበኛ ወጪ | **280.7** | **363.6** | **518.3** | **61.4** | **30.0** |
| ካፒታል ወጪ | **207.6** | **235.4** | **267.2** | **38.6** | **15.2** |
| **የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ** | 295.14 | 342.5 | 387.5 | **100.0** | **17.0** |
| ትምህርት | 123.1 | 141.2 | 169.4 | 42.0 | 18.1 |
| ጤና | 51 | 63 | 68.4 | 17.7 | 21.6 |
| ግብርና | 40.3 | 50.3 | 48.5 | 13.6 | 9.5 |
| ውሃ | 26.7 | 24.8 | 38.3 | 8.6 | 20.0 |
| መንገድ | 54.04 | 63.2 | 62.9 | 18.8 | 16.0 |

በመሆኑም ባለፉት ዓመታት የካፒታል በጀት ድርሻ እየቀነሰ የመደበኛ ድርሻ እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከኮቪድ ወረርሽኝ እና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከተከሰተው ጦርነት በተጨማሪ፣ የመንግስት የአገር ውስጥና የውጭ ዕዳ ክፍያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨረ መምጣት የመደበኛ ወጪውን ድርሻ እያሳደገው ሊሄድ ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት እንኳን የድህነት ተኮር ወጪ ድርሻ መጨመር መንግሥት ለፖሊሲው ያለውን ቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

## 3.1.3 የበጀት ጉድለት እና የመንግስት ዕዳ ሁኔታ

የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ካካተታቸው የፊሲካል ሪፎርሞች መካከል አንዱ የመንግስትን የፊሲካል ጉድለት እና አሸፋፈን ዘላቂና የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን በሚያሰፍን እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በ2010 በጀት ዓመት የፊሲካል ጉድለቱ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ከነበረበት የ3 በመቶ ድርሻ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 2.5 በመቶ ማውረድ ተችሎ ነበር፡፡ ከዚህም ባለፈ ይህን የበጀት ጉድለት በአብዛኛው ከመንግሰት ግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ በተገኘ የአገር ውስጥ ብድር እና የውጭ ብድር የተሸፈነ ሲሆን፣ ከብሔራዊ ባንክ የሚወሰደውን የቀጥታ ብድር በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ተችሎ ነበር፡፡ ሆኖም ከ2012 ጀምሮ ከወረርሽኙ፣ ከተፈጥሮ አደጋ እና ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ በተፈጠረው የፊሲካል ጫና ምክንያት የበጀት ጉድለቱ እየሰፋ የሄደ ሲሆን፣ በተለይ በ2014 በጀት ዓመት 4.2 በመቶ ሊደርስ ችሏል፡፡ በተለይም ለመንግስት በጀት ጉድለት መሸፈኛ ከብሔራዊ ባንክ በቀጥታ የተወሰደው ብድር ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ይህም የበጀት ጉድለቱን ለመሸፈን የተወሰደው ብድር በያዝነውም ሆነ በቀጣዮቹ ዓመታት የሚኖረውን የብድር ክፍያ ወጪ ፍላጎት እንዲጨምርና የፊሲካል

ሥፍራው (fiscal space) እየጠበበና የፊሲካል ጫናውም እንዲጨምር እያደረገ መምጣቱን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡

የመንግስት ዕዳ ክምችትን /debt stock/ ከመቀነስ አንጻር የኤክስፖርት አፈጻጸማችን ተሻሽሎ የሀገሪቱ የመንግስት ዕዳ የስጋት ደረጃ ከከፍተኛነት ወደ መካከለኛ ደረጃ እስከሚሻሻል ድረስ አዳዲስ የንግድ የውጭ ብድሮች እንዳይወሰዱ የሚከለክለውን መመሪያ ተግባራዊ ከማድረግ ጀምሮ የዕዳ ሽግሽግ ድርድሮችን በማድረግ የውጭ ዕዳ ክምችት እንዳይጨምር ማድረግ የሚያስችሉ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ የሀገር ውስጥ ዕዳም ቢሆን እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ለመንግስት ዕዳ እንደ ስጋት ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ሆኖም ከጦርነቱ ጋርም በተያያዘ የመንግስት ወጪ ከፍተኛ ጭማሪ በማሳየቱና የመንግስትም ገቢ መቀነስ ጋር ተያይዞ መንግስት በዕቅድ የያዛቸው የልማት ፕሮጀክቶች ትግበራ ከመስተጓጎሉም በላይ የመንግስት የሀገር ውስጥ ዕዳ ክምችትና የብድር ክፍያ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይሄንን ጉዳይ እንደ አንድ የፊሲካልና የኢኮኖሚ ስጋት በመውሰድ ስጋቱ ወደ ኢኮኖሚ አደጋነት እንዳይቀየር ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን የፊሲካል እርምጃ መውሰድ ተገቢ ይሆናል፡፡ በሌላም በኩል ከወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ ጋር በተያያዘ የዓለም ዓቀፍ ማህበረሰብ በሀገሪቱ ላይ ባደረሰው ጫና የውጭ ዕዳ ሽግሽግም እንደተጠበቀው ባለመሄዱ የውጭ ዕዳ ክፍያ ጫናም ከፍተኛ ስጋት ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚው አፈጻጸም ግምገማ እንደሚያሳየው አገራችን ከገጠሟት ውጫዊና ውስጣዊ ተግዳሮቶች ሳቢያ ያለባት የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ችግር ዳግም ተከስቷል፡፡ ስለዚህም የቀጣዮቹ ዓመታት የፊሲካል ፖሊሲ ማዕቀፍ ዝግጅት ይህንን እውነታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን፤ ትኩረቱም ይህንን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን በቶሎ ለማስተካከል የሚያስችሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ማስቀመጥ ላይ ተደርጓል፡፡

### 3.1.4 የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር

የመንግስትን የፊሲካል ፖሊሲ በውጤታማነት ተግባራዊ ለማድረግ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ችግር ፈች የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ይታመንበታል፡፡ በዚህ ረገድ ውጤታማ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን በሥራ ላይ ማዋል የህዝብን ሀብት በአግባቡና ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው ሥርዓት መምራት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ እነዚህን

ተግባራት የሪፎርም ፕሮግራም በመቅረጽ ወጥነት ባለው መንገድ ሥራ ላይ ለማዋል ተሞክሯል፡፡ ይህ የሪፎርም ፕሮግራም በበጀት፣ በክፍያ፣ በሂሳብ፣ በውስጥና በውጭ ኦዲት እንዲሁም በፋይናንስ መረጃ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ዘመናዊና ቀልጣፋ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ አገር አቀፍ አሰራሮችን ለመዘርጋት አስችሏል፡፡ ከነዚህም የተከናወኑ ተግባራት መካካል:-

- የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር የህግ ማዕቀፍ በማሻሻል ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ም/ቤት ከታየ በኂላ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለውሳኔ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም የአዋጁ ማስፈፀሚያ ረቂቅ መመሪያዎች ተረቀው የአዋጁ መጽደቅ እየተጠበቁ ነው፡፡ የመንግስት ግዥ ስርዓትን በማዘመን ቀልጣፋ፣ ግልፅና ውጤታማ ግዥዎችን ለማከናወን እንዲረዳ የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ ስርዓት ለምቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በዚህም መሰረት የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት (Electronic Government Procurement) በ73 የፌደራል መ/ቤቶች ላይ ትግበራ ተካሂዷል፡፡ በቀጣይ በጀት ዓመት ስርዓቱ በሁሉም የፌደራል መ/ቤቶች ተግባራዊ ይሆናል፡፡

- በመንግሥት ክፍያ፣ በመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር እና በውስጥ ኦዲት አሰራር ላይ የማስፈፀም አቅም በማሳደግ ጥራት ያለው ሪፖርት እንዲቀርብ ከማድረግ አንፃር ከፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ለተወጣጡ 280 ሴቶች 268 ወንዶች በድምሩ 548 የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ባለሙያዎች በሲቪል ሰርቪስ ዩንቨርሲቲ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ተቋማዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለ1156 ባለሙያዎች መሠረታዊ የኢፍሚስ አጠቃቀም እንዲሁም አዲስ በተዘጋጀው የውስጥ ኦዲት ማንዋል ላይ ለ507 የውስጥ ኦዲተሮች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የኢትዮጵያ ሂሣብ ባለሙያዎች ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ በማዘጋጀት ለውሳኔ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቧል፡፡ ዓለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎችን (IPSAS) ትግበራውን በበላይነት የሚመራ የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴ ተቋቋሞ ቀጣይ ስራዎችን ለማከናወን ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

- ዜጎች ስለሀገራዊ በጀት ዝግጅት ሂደትና መረጃ አውቀውና ተረድተው በበጀት ትግበራ ሂደት ላይ በባለቤትነት እንዲሳተፉና እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ በህግ አውጭው አካል ለ2015 በጀት ዓመት የፀደቀውን በጀት ለሁሉም ዜጎች በቀላልና ሊገባ በሚችል መልኩ

አዘጋጅቶ ለማሠረጨት በታቀደው መሠረት የዜጎች የበጀት መረጃ ሠነድ (Citizens Budget) ተዘጋጅቶ መረጃው ተሰራጭቷል፡፡ በሌላም በኩል ኢትዮጵያ የበጀት ስርዓት ግልፅነት ደረጃ ለመለካት የሚያችል ዳሰሳ 2ኛ ዙር ጥናት በዓለም አቀፍ የበጀት አጋርነት ድርጅት ተካሄዶ ውጤቱ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

- የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ለማሻሻል የተለያዩ የማቴርያል እና ቴክኒክ ድጋፎች ተደርጓል፡፡

# 4. የ2015 በጀት አፈጻጸም ዕይታ

## 4.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ አፈጻጸም

**የኢኮኖሚ ዕድገት**:- ቀደም ሲል በመገባደድ ላይ ባለው 2015 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው የ9.2 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ግብ መያዙ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በዓለም ዓቀፍ ሁኔታ በተከሰተው ከፍተኛ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ምክንያት፣ እንዲሁም በሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ምክንያት የአለም የንግድ ሰንሰለት መዛባት እና የመሳሰሉት ምክንያቶች እንዲሁም ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው መጠነ ሰፊ ጦርነት ያስከተለው የኢኮኖሚ እና የፊሲካል ጫና አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ቀደም ሲል ከተገመተው በታች ሊሆን እንደሚችል ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ በመሆኑም መንግስት እና ባለድርሻ አካላት እያደረጉት ባለው ርብርብ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ የማይበገር በመሆን የ7.5 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በ2016 በጀት ዓመት 7.9 በመቶ ዕድገት እንደሚመዘገብ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

**የሸቀጦች የወጪ ንግድ:-** በመገባደድ ላይ በሚገኘው 2015 በጀት ዓመት የሸቀጦች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም አንጻር ሲታይ ቅናሽ አሳይቷል፡፡ በዚህም መሰረት በ2015 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ከሸቀጦች የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) 2376.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህም በ2014 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተገኘው 2522.8 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ጋር ሲነፃጸር በ146.7 ሚሊዮን ዶላር (በ5.8 በመቶ) ያህል ቅናሽ ማሳየቱን መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም በመጠን ሲታይ እንደዚሁ ከባለፈው ዓመት አንጻር መጠነኛ ቅናሽ ማሳየቱን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ በመሆኑም በቀሪዎቹ ወራት ወጪ ንግዱን ላማሻሻል መሰራት ያለበትን ሁሉ በማድረግ አፈጻጸሙን ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡

**የዋጋ ንረት፦** በመጋቢት ወር 2015 ዓ.ም የተመዘገበው የ12 ወራት አማካይ (12 Months Moving Average) አገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ዕድገት 33.7 በመቶ መሆኑን የዋጋ ናሙና ዳሰሳ ጥናት አመላክተዋል፡፡ የዚህ ዕድገት ምንጭ ምግብና ምግብ ነክ ባልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ ሲሆን፣ የምግብ ነክ የ12 ወራት አማካይ አገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ዕድገት 34.5 በመቶ ሲሆን፣ የምግብ ነክ ያልሆኑ ዕቃዎች የዋጋ ግሽበት 32.5 በመቶ ሆኗል፡፡

## 4.2 የ2015 በጀት የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም

በያዝነው 2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ብር 786.61 ቢሊዮን በጀት ያጸደቀ ሲሆን ይህንንም ወጪ ከሐምሌ 2014 ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህንን ወጪ ለመሸፈን ብር 477.78 ቢሊዮን ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢ እንዲሁም ከውጭ ዕርዳታ ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን፤ በዚህም የበጀት ጉድለቱን ብር 308.83 ቢሊዮን ያደርሰዋል፡፡ የበጀት ጉድለቱም በብር 42.6 ቢሊዮን የውጭ ብድር እና ብር 266.07 ቢሊዮን ደግሞ ከአገር ውስጥ ብድር ለመሸፈን ታሳቢ ተደርጎ የጸደቀ በጀት ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት የፌዴራል መንግሥት የተጣራ ታክስ ገቢ ብር 282 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም በበጀት ዓመቱ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ብር 400.2 ቢሊዮን የታክስ ገቢ አንጻር የ70.5 በመቶ አፈጻጸም አሳይቷል፡፡ የታየው የታክስ ገቢ አሰባሰብ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር በመጠነኛ ወደኋላ የቀረ ቢሆንም፤ በ2014 ተመሳሳይ ጊዜ ከተሰበሰበው ገቢ ጋር ሲነጻጸር የ26.7 በመቶ ዕድገት ሊያሳይ ችሏል፡፡

በወጪ ረገድ በ2015 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ለፌዴራል መንግሥት መደበኛ፣ ካፒታልና ለክልሎች ጠቅላላ የበጀት ድጋፍን ጨምሮ በድምሩ ብር 458.0 ቢሊዮን ወጪ ተደርጓል፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ክፍያ ለመፈጸም ከታቀደው ብር 755.34 ቢሊዮን /የፕሮጀክት ዕርዳታ ሳይጨምር/ ጠቅላላ ወጪ ጋር ሲነጻጸር የ60.6 በመቶ አፈጻጸም ያሳየ ሲሆን፤ በ2014 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው የወጪ አፈጻጸም ጋር ሲነፃፀርም የ26.9 በመቶ (የብር 97.1 ቢሊዮን) ብልጫ አለው፡፡

በአጠቃላይ በተያዘው በጀት ዓመት የገቢውም ሆነ የወጪ ፍሰት በጥሩ የፊሲካል ዲሲፕሊን እየተመራ መሆኑንና በተቀሩትም ወራቶች የተለየ የወጪ ፍላጎት ኖሮ ካልተዛባ በስተቀር የተሻለ የፊሲካል አፈጻጸም ሊኖር እንደሚችል ይገመታል፡፡

ሆኖም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተከሰተው ጦርነት ከፍተኛ የሰብዓዊና የኢኮኖሚ ጉዳት በማድረሱ በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሃት አመራሮች መካከል የተደረገውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በጦርነቱ ለተጎዱ ማኅበረሰቦች ተጨማሪ የሰብአዊ ድጋፍ እንዲሁም በጦርነቱ የወደሙ ከተሞችን መልሶ ለማቋቋም ተጨማሪ የወጪ ፍላጎት ሊያስከትል እንደሚችል ይገመታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ጦርነቱ በስምምነት እስከተቋጨበት ጊዜ ድረስ ባሉት የበጀት ዓመቱ ጥቂት ወራት በተዘዋዋሪ መንግስት ለመሰብሰብ በያዘው የገቢ ዕቅድ አሰባሰብ ላይ የራሱን ተፅዕኖ ማሳደሩን መገመት አያዳግትም፡፡ በዚህም ጦርነቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን

በማዳከሙና ጦርነቱ በነበረባቸው አካባቢዎች ያሉ የኢኮኖሚ ተቋማት በመውደማቸውም ሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማቆማቸው ከነዚህ አካበቢዎች ለመሰብሰብ የተያዘውን ገቢ በዕቅዱ መሰረት ለመሰብሰብ አዳጋች ሊሆን እንደሚችል የሚገመት ቢሆንም በቅርቡ የተደረገው የሰላም ስምምነት ጦርነቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የገቢ አሰባሰብ ላይ የተወሰነም ቢሆን አወንታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይህንንም ተከትሎ መንግስት በአሁኑ ጊዜ ከአለም ባንክ፣ ከአለም ዓቀፍ የገንዘብ ድርጅት እና ከሌሎች አካላት ጋር እያደረገዉ ባለዉ ውይይት ለወደፊት ከልማት አጋሮች ጋር ያለው ድጋፍን እንደሚያሻሽል ይገመታል፡፡

ጦርነቱ በያዝነው በጀት ዓመትና በቀጣዮቹ ዓመታት ከፍተኛ የፊሲካል ጫናንና ስጋትን እንደሚያስከትል ሳይታለም የተፈታ ችግር መሆኑ ቢታወቅም፤ የተካሄደውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በፊሲካል አፈጻጸሙም ሆነ በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ ስለሆነም የቀጣዩም ዓመት የመንግስት በጀት ዝግጅት ዋና የትኩረት አቅጣጫ ይህንን እየታየ ያለውን የፊሲካል ሚዛን መዛባት ለማስተካከል ትኩረት የሚሰጥ መሆን የሚገባው ሲሆን አፈጻጸሙንም በቅርበት መከታተል ይጠበቃል፡፡

## 5. የ2016 በጀት ዓመት ገቢ፣ ወጪና የወጪ አሸፋፈን

ከዚህ በላይ በቀረቡት የሰነዱ ክፍሎች ከአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም አንጻር የተገኙ ዋና ዋና ስኬቶችን፣ እንዲሁም የ2015 በጀት ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚና የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም ዕይታ በሚመለከት በዝርዝር ተዳሰዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ጉዳዮች ከግምት ባስገባ መልኩ የ2016 በጀት ዓመት ዓመታዊ በጀቱ የተዘጋጀ ሲሆን በዋናነትም ባለፉት ዓመታት በተፈጠሩ ውጣ ውረዶች ምክንያት የተዛባውን ማክሮ ኢኮኖሚ የማስተካከል ዓላማን ሰንቆ ነው ፡፡

ተፈጥሮ የነበረውን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ለማስተካከል መንግስት ዘርፈ ብዙ እርመጃ እየወሰደ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የኢኮኖሚ መሻሻያ በመንደፍ ተፈጻሚ ሲሆን ቆይቷል፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ባጋጠሙ ዓለም አቀፍ ተግዳሮቶች ምክንያት ቀላል የማይባሉ ሀገሮች ኢኮኖሚያቸው የኳልዮሽ ጉዞ በሚያደርግበት ሁኔታ የሀገራችን ኢኮኖሚ ሳይበገር ወደፊት እንዲሄድ አስችሎታል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም የዚሁን ማሻሻያ ቀጣይ ክፍል በማዘጋጀት ከሚቀጥለው በጀት ዓመት ጀምሮ መተግበር እንደሚጀምር ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ልንከተላቸው የሚገቡ የፖሊሲ አቅጣጫዎችም ሆኑ የመንግስት በጀት ዝግጅት ከዚህ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የፊሲካል ፖሊሲው አቅጣጫ ከላይ የተካተቱትን ማሻሻያዎች ተግባራዊ ከማድረግ ባለፈ የመንግስት በጀት አሁንም ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለመንገድ መሠረተ ልማት፣ ለግብርናና መስኖ፣ ለንጹህ መጠጥ ውሃ

አቅርቦት እና በቀጣይ አዲስ ትኩረት ለሚሰጣቸው ዘርፎች ቅድሚያ የሚሰጥ ይሆናል። ሆኖም በነዚህ ዘርፎች ውስጥ የየትኞቹ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሄድ እንደሚገባው መንግስት የፖሊሲ አቅጣጫ ማስቀመጥ የሚገባው ሲሆን፣ ይህም በዝርዝር የበጀት ዝግጅት ወቅት ለማየት ተሞክሯል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለፉት ዓመታት መንግሥት በተለይ ለማህበራዊ ዘርፍ በተለይም ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና የልዩ ልዩ ሙያ ማሰልጠኛዎች የሚመረቁ ዜጎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ማደጉ አንድ ጉዳይ ሆኖ፣ ይህንን የሰለጠነውን የሰው ሀይል ሀገሪቱ ባግባቡ እየተጠቀመችበት ነው ወይ የሚለው ጉዳይ በአንክሮ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

በመንግሥት ገቢ አሰባሰብ ረገድም የታክስ ገቢን ለማሻሻል ዜጎችን በማሳተፍ እና የታክስ ሰብሳቢ ተቋማትን አቅም በማጠናከር፣ ዘመናዊ አስተዳደር በመዘርጋትና የታክስ ትራንስፎርሜሽንን በማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሰራ እምነት ተጥሏል። በአንጻሩም የፊሲካል ሥርዓቱን ለማጠናከር የመንግስት ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነትን የሚያሻሽሉ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ ሥርዓቶችን በመዘርጋትና በውጤታማነት ሥራ ላይ በማዋል የሀብት ብክነትን ለማስወገድና በጀትን በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችሉ ተግባራት የማከናወኑ ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ ቀጣይ ይሆናል። ይህም የመንግስትን ውስን ሀብት በአግባቡና በውጤታማነት በመጠቀም የማህበራዊና ኢኮሚያዊ አገልግሎቶችን፣ አቅም በፈቀደ መጠን ለህብረተሰቡ ለማድረስ የሚያስችል ይሆናል። እንደ ባለፉት ዓመታት የ2016 በጀት ዝግጅት እነዚህን ማሻሻያዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንዲሁም በቀጣዮቹ ዓመታት ዕውን ይሆናሉ የተባሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕይታዎችን ታሳቢ በማድረግ ለማዘጋጀት ተሞክሯል።

## 5.1 ኢኮኖሚያዊና ፊሲካል ታሳቢዎች

### 5.1.1 ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች

በሀገራችን የሰሜኑ ክፍል የነበረውን ጦርነት ለማስቆም መንግስት የፈጸመውን ቁርጠኛ የሰላም ስምምነት ከሁሉም በላይ በቀጣዮቹ ዓመታት በሀገራችን ሰላም እንደሚሰፍንና ዘመኑም ኢኮኖሚውን መልሶ በመገንባት ላይ ትኩረት በመስጠት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ከተግዳሮቶች የተላቀቀና ለቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት ምቹ ሁኔታዎች እንደሚፈጠር ታሳቢ በማድረግ፣ ለ2016 በጀት ዓመት ዝግጅት የሚከተሉት ዋና ዋናና ተያያዥ የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ተደርገዋል።

- በዘንድሮ በጀት ዓመት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሀገራችን ህግ ማስከበርንና የህልውና ዘመቻን ተከትሎ በተከሰተው ሁኔታ ኢኮኖሚው በመዳከሙ፣ የመንግስት ገቢ በመቀነሱ፣ ከልማት አጋሮች የሚገኙት የበጀትና ልማት ድጋፍ በመቋረጡ እንዲሁም ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ በበርካታ አካባቢዎች በርካታ ህዝብ በመፈናቀሉ እንዲሁም የተለያዩ የኢኮኖሚ ተቋማት በመውደማቸው ወይም ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውጭ በመሆናቸው፣ ከፍተኛ ሀብት ለጦርነቱ በመዋሉ የመንግስት የፊሲካል አቅም የተዳከመ ከመሆኑም በላይ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽእና እንደሚፈጥር ግልጽ ነው፡፡ እንዲሁም በተወሰኑ የሀገራችን የአርብቶ አደሩ አከባቢዎች የተከሰተው መጠነ ሰፊ የሆነ ድርቅ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ሲሆን፣ ይህም በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ምንም እንኳን የግብርና እምቅ ሀብት ባላቸው አካባቢዎች እነዚህ ጉዳቶች በኢኮኖሚው ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ ለማካካስ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ቢሆንም ጉዳቱን ሙሉ ለሙሉ ማካካስ የሚቻል ባለመሆኑ በያዝነው የ2015 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው ቀደም ብሎ ያድጋል ተብሎ ከተያዘው የ9.2 በመቶ ዕድገት ዝቅ ያለ ምጣኔ ሀብት 7.5 በመቶ ዕድገት እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- የዋጋ ንረት ለማዕቀፉ ዝግጅት የተወሰደ ሌላኛው የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት የዋጋ ንረቱ በሁለት አሀዝ የሚለካ መሆኑ ለማክሮ-ኢኮኖሚው መረጋጋት ትልቅ ፈተና ሆኖ እንደቀጠለ ነው፡፡ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የዋጋ ንረቱን በያዝነው በጀት ዓመት ወደ ነጠላ አሃዝ ማውረድ አዳጋች እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- የገቢ ዕቃዎች ዋጋ (Value of goods import) በ2015 በጀት ዓመት የ7.2 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ በ2016 በጀት ዓመት የ18.9 በመቶ አማካይ ዕድገት እንደሚመዘገብ ትንበያው ያሳያል፡፡ ይህም ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለሚሰበሰበው የመንግስት ገቢ ግምት መሰረት ነው፡፡
- ኢኮኖሚው ጦርነቱ ካደረሰው ጫና አንጻር ለማገገም የተወሰኑ ዓመታትን የሚጠይቅ በመሆኑ ቀድሞ በታቀደው ልክ የልማት ዕቅዶችን ለማስፈጸም ተግዳሮት መሆኑ አይቀርም፡፡ ከጦርነቱ ጋርም ተያይዞ የገጠመውን ከፍተኛ ወጪ ለመሸፈን ሲባል የተከሰተውን የፊሲካል ሚዛን መዛባት በመካከለኛ ዘመን ጊዜ ውስጥ የተመጣጠነ ለማድረግ የዕዳ ክፍያ ላይ ትኩረት ማድረግ የግድ የሚል ሲሆን፣ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ካለው የፋይናንስ ፍላጎት አንጻር የልማት ሥራዎች በተወሰነ ደረጃ መጓተት

የሚያጋጥም በመሆኑ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የማሳደር ስጋት መኖሩን ግምት መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡

## 5.1.2 የፊሲካል ፖሊሲ ታሳቢዎች

መንግስት በሀገሪቱ የተከሰተውን የተዛባ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን ለማስተካከል ይረዳል ተብሎ የታመነበትን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ በማድረጉ ተስፋ ሰጪ የኢኮኖሚ ለውጦች መታየት መጀምራቸውን መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ ሆኖም ከ2012 አጋማሽ ጀምሮ በሀገራችን የተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍል ተከስቶ የነበረው የአንበጣ መንጋ፣ ድርቅ እና የጎርፍ አደጋ፣ እንዲሁም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተከሰተው የህግ ማስከበር ጦርነትና ተያያዥ አለመረጋጋቶች በኢኮኖሚው ላይ ተደራራቢ ጫናዎችን ፈጥረዋል፡፡ ነገር ግን ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ የተደረጉ መጠነ ሰፊ ማሻሻያዎች ኢኮኖሚው ይህ የደረሰበት ጫና ያስከተሉትን ተጽእኖዎች መቋቋም መቻሉን ግን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ጫና የበለጠ እየታየ ያለው ደግሞ በመንግስት የፊሲካል አቅም ላይ ነው፡፡ ጫናው ከመንግስት ገቢ አንጻር የታክስ ገቢ አሰባሰብ የተጠበቀውን ያህል አፈጻጸም እንዳያሳይ አድርጓል፡፡ እንዲሁም፣ የልማት አጋሮች የሚሰጡትን የልማት ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሱ ሲሆን፣ በተለይም በበጀት ድጋፍ መልክ የሚሰጡትን ድጋፍ ሙሉ ለሙሉ አቁመዋል፡፡

የ2016 በጀት ዋነኛ ዓላማ ባለፉት ዓመታት የተከሰቱት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቀውሶች እንዲሁም ቀደም ባሉ ዓመታት መንግስት የልማት ፕሮጀክቶቹን ፋይናንስ ለማድረግ የተከተለው አካሄድ ያስከተለውን የፊሲካል መዛባት በማስተካከል የፊሲካል ጤናማነትን እውን ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ በጀት በቀርቡ ስራ ላይ ከሚውለው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለት ኢላማዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን በዋናነትም አሁን የሚታየውን የተዳከመ የፊሲካል አቋም አስተማማኝ ደረጃ ላይ ማድረስ የሚቻለው አስተማማኝ ከሆነው የመንግስት ታክስ ገቢ ምንጭ የገቢ አሰባሰብ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ አማራጭ የሌለው መሆኑን ከግምት ተወስዷል፡፡ ለዚህም የታክስ ገቢ አሰባሰብ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሥራዎችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የሁለተኛውን የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ለማስፈፀም የሚያግዝ የሦስት ዓመት ዝርዝር የፐብሊክ ኢንቨስትመንት ዕቅድ እየተዘጋጀ ስለሆነ የወጪ ታሳቢዎቹ የማሻሻያውን እና የኢንቨስትመንቱን ዕቅድ ማዕከል

ያደረጉ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ለበጀቱ ታሳቢ የተደረጉ የገቢና ወጪ ታሳቢዎች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 5.2 የፌዴራል መንግሥት የገቢ ታሳቢዎች

የፌዴራል መንግስት ገቢ ከሶስት ዋና ዋና ምንጮች የሚገኝ ሲሆን፣ እነዚህም የታክስ ገቢ፣ ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች እና የውጭ ዕርዳታ የገቢ ምንጮች ናቸው፡፡ በመሆኑም የ2016 በጀት ከነዚህ ምንጮች ሊገኝ የሚችለውን የፌዴራል መንግስት ገቢ ለማስላት የተለያዩ ታሳቢዎች የተወሰዱ ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- **የ2015 በጀት ዓመት የታክስ ገቢ ዕቅድ አፈጻጸም፡-** የፌዴራል መንግስት በ2015 በጀት ዓመት ከታክስ ምንጭ ብር 400.2 ቢሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በዚህም በጀት ዓመት የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ውስጥ የተሰበሰበው የተጣራ የታክስ ገቢ ብር 282.1 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም የዓመታዊ ዕቅዱ 70.5 በመቶ መሰብሰቡን ያሳያል፡፡ ከዚህ በመነሳት በበጀት ዓመቱ ብር 52.0 ቢሊዮን የሚደርስ የታክስ ገቢ ላይሰበሰብ እንደሚችል ወይም የዓመታዊ ዕቅዱ 87 በመቶው (ብር 348.0 ቢሊዮን) ብቻ ሊሰበሰብ እንደሚችል ተገምቷል፡፡ በመሆኑም የ2015 የታክስ ገቢ አፈጻጸም ለ2016 የታክስ ገቢ ግምት እንደመነሻ ተወስዷል፡፡
- **የክልሎች የጋራ ገቢ ድርሻ ከፍተኛ እየሆነ መምጣት በሚሰበሰበው የፌዴራል ገቢ ድርሻ ላይ የሚኖረው እንደምታ፡-** በያዝነው በ2015 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በፌዴራል መንግስት ተሰብስቦ ለክልሎች የተላለፈው የጋራ ገቢ ድርሻ ብር 42 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን፣ ይህም በ2014 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ተሰብስቦ ከተላለፈው አንጻር በ47 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህም ከፌዴራል መንግስት የሚታጣው የገቢ ድርሻ ከተጠበቀው በላይ በመሆኑ የፌዴራል መንግስት ገቢ እየቀነሰ መሄዱን ያሳያል፡፡ ስለሆነም ይህ እውነታ የቀጣዮቹ ዓመታት የፌዴራል መንግስት የታክስ ገቢ ግምት ሲዘጋጅ ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- **የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ለታክስ ገቢ ትንበያ ያላቸው እንደምታ፡-** ከላይ የተገለጹት የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎችና ሊኖር የሚችለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለታክስ ገቢ አቅም በየታክስ ዓይነቱ (የቀጥታ ግብርና ታክስ፣ የአገር ውስጥ ኤክሳይዝና ተጨማሪ እሴት

ታክሶችና የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ፣ ኤክሳይዝ፣ ተ.እ.ታ. እና ሱር ታክሶች) የሚኖራቸው እንደምታ በዝርዝር በትንበያ ሞዴሉ እንደዋነኛ ታሳቢ ተደርጓል፣

- **የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያ ታሳቢዎች፡** ከያዝነው በጀት ዓመት ጀምሮ ለፓርላማ ቀርበው እንደሚጸድቁና ሥራ ላይ እንደሚውሉ የሚጠበቁ የታክስ ህጎች በቀጣዮቹ በጀት ዓመታት ለታክስ ገቢ አሰባሰቡ የሚኖራቸውን ተጨማሪ አቅም ከግምት ውስጥ ገብቷል። ከያዝነው በጀት ዓመት ጀምሮ የቀረቡትን የታክስ ህግ ማሻሻያዎች ተግባራዊ በማድረግ በ2016 በጀት ዓመት ብር 93.1 ቢሊዮን ተጨማሪ የታክስ ገቢ መሰብሰብ ይቻላል የሚል ግምት ተወስዷል። በቀጣዮቹ ዓመታት ማሻሻያዎቹን የበለጠ አጠናክሮ ተግባራዊ በማድረግም የበለጠ የታክስ ገቢ መሰብሰብ እንደሚቻል በማሰብ የተለጠጠ ዕቅድ ተይዟል። በመሆኑም እነዚህን በሥራ ላይ ለማዋል የታቀዱት ዋና ዋና የታክስ ህጎች የሚከተሉት ናቸው፣

  - ✓ **የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ**፡- ታክሱ ሊጣልባቸው የሚገባ ወደ ታክስ መረቡ እንዲገቡ በማድረግ፣ እንዲሁም አዳዲስ አገልግሎቶችና ዕቃዎች እንዲካተቱ በማድረግ ከተ.እ.ታ. ምንጭ የሚሰበሰበው ከሀገር ውስጥ ምርት አንጻር 1 በመቶ ገቢውን እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል።

  - ✓ **ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፡-** ይህ ማሻሻያ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በቅንጦት ዕቃዎች እንዲሁም ለጤና ጥሩ ያልሆኑ ምርቶች ፍጆታ በመቀነስ በጤና ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋ መቀነስ ነው። ታክሱ የሚጣለው በተወሰኑ ዕቃዎች፣ ተሽከርካሪዎች እና አገልግሎቶች በመሆኑ በቀጣይ አመታት ገቢውን በ10 ቢሊዮን ብር እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል።

  - ✓ የኤክሳይዝ ቴምብር (Excise Stamp, and Track and Trace System)፡- ኤክሳይዝ የተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰብ ገቢ ሲሆን ይህም ተግባራዊ ሲደረግ ህገ-ወጥ ንግድን በማስቀረት ወይም በመቀነስ (በሲጋራ እና አልኮልና የአልኮል ውጤቶች በተለይ) ከኤክሳይዝ ታክስ ሊገኝ የሚችለው ገቢ በ30 ቢሊዮን ብር ሊጨምር እንዲሚችል ታሳቢ ተደርጓል።

  - ✓ የማህበራዊ ዋስትና ልማት ቀረጥ፡- ከፍትሐዊነት አንጻር ሲታይ በተለይ የሱር ታክስ በተወሰኑ ዕቃዎች የሚጣል ከመሆኑ በላይ ከሌሎች ታክስች ቀጥሎ በመጨረሻ የሚጣል በመሆኑ ከፍተኛ የጉምሩክ ቀረጥ የከፈለ ይበልጥ ከፍተኛ ሱር ታክስ እንዲከፍል የሚያደርግ ሲሆን ቀረጥ የማይከፈልበት ዕቃ ሱር ታክስ እንዳይከፈልበት የሚያደርግ ነበር። በመሆኑም የማህበራዊ ዋስትና ቀረጥ በሁሉም ገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጣል ታክስ ሲሆን ይህም ገቢውን እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል።

- ✓ የንብረት ታክስ (Property Tax) ህግ፡- አዲስ የንብረት ታክስ ህግ ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን ከዚህ የሚገኘውም ገቢ ሙሉ በሙሉ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች እንደሚሆን ተወስኗል:: ለዚህም ታክስ ትግባራ ሌሎች ህጎች ጸድቆ ተግባራዊ እንደሚሆኑና ይህም የታክስ መሰረቱን እንደሚያሰፋና የታክስ ገቢ በተለይም የክልሎችን ገቢን እንደሚጨምር ግምት ተወስዷል፡፡

- **የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች፡-** የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት የሰው ሀይልና ተቋማዊ አቅምና የአሠራር ችግሮችን እና አደረጃጀቱን በጥልቀት በመፈተሽ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዚህም በተግባር ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ በመንግስት በኩል ቁርጠኝነት እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ነገር ግን ግብርና ታክስ የማይከፍሉ የተለያዩ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዘርፍ ውስጥ የሚሳተፉ የኢኮኖሚ ተዋናዮችን በግብር ሥርዓቱ ማስገባት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ማሻሻያ ማካሄድ አስፈላጊ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች ታሳቢዎች

በቀጣዮቹ ዓመታት ታክስ ካልሆኑ ምንጮች የሚሰበሰቡት ገቢዎች በዋናነት ከመንግስት የልማት ድርጅቶችና ከሌሎች ተቋማት ከሚገኘው የዘቀጠ ትርፍ ገቢ፣ በባለበጀት መ/ቤቶች ከሚሰጡ አገልግሎቶች ክፍያ፣ ከመንግስት ዕቃዎች ሽያጭ እና ከመሳሰሉት ከሚገኙ ገቢዎች ነው፡፡ በቀጣዮቹ ዓመታት ትልልቅ ገቢዎች ከሚሰበሰብባቸው ምንጮች ሊገኙ የሚችለው ገቢ መጠንን የሚያሳይ ግምት መረጃ ከየተቋማቱ የተገኘ ሲሆን፣ ከበርካታ ተቋማት የሚሰበሰቡ ጥቃቅን ገቢዎችን ደግሞ ባለፉት ዓመታት የተሰበሰበውን ገቢ መረጃ በመጠቀም (trend forecast) ለመገመት ተሞክሯል፡፡

## የውጭ ዕርዳታና ብድር (soft loan) ዋና ዋና ታሳቢዎች

የውጭ ሀብት ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር እንዲሁም በቀጥታ ወደ ትሬዠሪ ከሚፈሱ ፕሮግራሞች የሚገኝ የዕርዳታ እና ብድር ሀብት ነው፡፡ በበጀት ውስጥ የተካተቱ የብድር ሀብቶች በረዥም ጊዜ የሚከፈሉ እንዲሁም ዝቅተኛ ወለድ እና ረጅም የመክፈያ ችሮታ ጊዜ ያላቸው የብድር ዓይነቶች ናቸው፡፡ ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር የሚገኙት ገቢዎች በቀጥታ ለፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ ብቻ የሚውሉ ሲሆን ከአስፈጻሚ አካላት በተገኘ የፕሮጀክቶች ዝርዝር መሠረት የተገመተ ነው፡፡ በአንጻሩ ወደ ትሬዠሪ በቀጥታ የሚፈሱት የብድርና ዕርዳታ ገቢዎች በልማት አጋሮች እና በመንግስት በተደረሱ ስምምነቶች መሠረት እንዲሁም፣ የፍሰት ታሪካቸውን በመገምገም የተገመተ ነው፡፡ ነገር ግን ከልማት አጋሮች የሚገኘው የገቢ ግምት

ምንም እንኳን ስምምነትን መሠረት ያደረገ ቢሆንም፣ ባለፉት ሶስት ዓመታት ከሰሜኑ የሀገራችን የሰላም ማስከበር ዘመቻ ጋር ተያይዞ ብድርና ዕርዳታ የቀነሰ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በያዝነው በጀት ዓመት በተደረሰው የሰላም ስምምነት ተከትሎ ከልማት አጋሮች የተሰጠው ምላሽ ጥሩ የሚባል በመሆኑ በቀጣይነትም ክትትል በማድረግ ከዚህ አንጻር ሊካተቱ የሚችል የውጭ ሀብት እንዲካተትና ለልማት ፋይናንሲንግ እንዲውል የሚደረግ ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡- የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት የገቢ ዕቅድ (በሚሊዮን ብር)**

| *የገቢ ዓይነት* | *2015* | | *የ2016 የገቢ ዕቅድ* | *ዕድገት በመቶኛ* | |
|---|---|---|---|---|---|
| | *በጀት* | *ግምት* | | *ከ2015 በጀት* | *ከ2015 ግምት* |
| ***ጠቅላላ ገቢና ዕርዳታ*** | ***477,775.28*** | ***407,606.58*** | ***520,606.46*** | **9.0** | **27.7** |
| ***የአገር ውስጥ ገቢ*** | ***438,851.32*** | ***376,787.75*** | ***479,486.79*** | **9.3** | **27.3** |
| ***የታክስ ገቢ ድምር*** | ***400,243.96*** | ***347,965.42*** | ***440,825.68*** | **10.1** | **26.7** |
| ***ቀጥታ ታክሶች*** | ***124,775.14*** | ***108,565.21*** | ***141,481.45*** | **13.4** | **30.3** |
| ***የአገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች*** | ***103,363.92*** | ***89,775.08*** | ***111,755.49*** | **8.1** | **24.5** |
| *የሀገር ውስጥ ዕቃዎች ተ.እ.ታ* | *36,707.90* | *31,882.06* | *39,688.02* | **8.1** | **24.5** |
| *የአገልገሎት ተ.እ.ታ* | *44,979.01* | *39,065.80* | *48,630.62* | **8.1** | **24.5** |
| *የዕቃዎች ኤክሳይዝ ታክስ* | *19,839.44* | *17,231.23* | *21,450.10* | **8.1** | **24.5** |
| *ተርን ኦቨር ታክስ* | *112.56* | *97.77* | *121,701.85* | **8.1** | **24.5** |
| *የቴምብር ሽያጭ ቀረጥ* | *1,725.01* | *1,498.23* | *1,865.05* | **8.1** | **24.5** |
| ***የውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ*** | ***172,104.90*** | ***149,625.13*** | ***187,588.74*** | **9.0** | **25.4** |
| *የጉምሩክ ቀረጥ /የገቢ ዕቃዎች/* | *62,238.79* | *54,109.37* | *67,226.62* | **8.0** | **24.2** |
| *የገቢ ዕቃዎች ኤክሣይዝ ታክስ* | *15,359.10* | *13,352.95* | *17,401.68* | **13.3** | **30.3** |
| *የገቢ ዕቃዎች ተ.እ.ታ* | *64,083.80* | *55,713.38* | *68,226.90* | **6.5** | **22.5** |
| *ሱር ታክስ* | *30,411.86* | *26,449.43* | *33,147.93* | **9.0** | **25.3** |
| ***ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች*** | ***38,607.36*** | ***28,822.33*** | ***38,661.11*** | **0.1** | **34.1** |
| ***ጠቅላላ የውጭ ዕርዳታ*** | ***38,924.16*** | ***30,818.83*** | ***41,119.67*** | **5.6** | **33.4** |
| *የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ድጋፍ* | *7,659.27* | *0* | *6,349.42* | **-17.1** | **-** |
| *የፕሮጀክቶች ዕርዳታ* | *31,264.69* | *30,818.83* | *34,770.25* | **11.2** | **12.8** |

## 5.3 የፌዴራል መንግስት ወጪ

በሀገራችን ካለው ከፍተኛ የልማት ፍላጎት አንጻር ክፍተት እንደመኖሩ መጠን የፌዴራል መንግስት የወጪ ፍላጎት ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም፣ የሚኖረውን ውስን የመንግስት ሀብት አሁን ከተፈጠረው የፊሲካል ጫና አንጻር ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው ለሚገቡ የወጪ ፍላጎቶች ማዋል አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የመንግስትን የወጪ ጣሪያ

ለመወሰን መንግስት የሚከተለውን የወጪ ፖሊሲ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና ሊኖር የሚችለውን የፋይናንስ አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ይዘጋጃል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል መንግስት የገቢ ሀብት ትንበያን መሠረት በማድረግ ለፌዴራል መንግስት መደበኛና ካፒታል ወጪዎች እንዲሁም ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት ድጋፍ እና የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ የሚያስፈልገው ወጪ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 5.3.1 የፌደራል መንግስት መደበኛ ወጪ

የመደበኛ ወጪ መንግስት ለሚከተለው ጤናማ የፊሲካል ጤናማነትን ማስፈን የፖሊሲ አቅጣጫ  አብዛኛው ለዕዳ ክፍያ የሚውል ሲሆን በጦርነቱ የወደሙ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞው ይዞታቸው ለመመለስ የመልሶ ማቋቋም ስራን ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የመደበኛ ወጪው አብዛኛው ለዕዳ ክፍያ፣ የሀገር ደህንነት ለማጠበቅ፣ በጦርነቱ እና በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ለተጎዱ ዜጎች የዕለት ዕርዳታ ለማቅረብ እና ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ ድጎማ ትኩረት የሰጠ ሲሆን ለመደበኛ ወጪ ከላይ ከተጠቀሱት መሠረታዊ ታሳቢዎች በተጨማሪ ከፕሮግራም በጀት አሰራር አኳያ ለሚጠበቁ ውጤቶችና ዋና ዋና ተግባራት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ወጪዎች በግምቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

በዚህም መሰረት ለ2016 በጀት ዓመት ብር 370.14 ቢሊዮን ለመደበኛ በጀት ወጪ ተደግፎ የቀረበ ሲሆን ይህም በ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው በብር 25.02 ቢሊዮን ወይም በ7.25 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡

## 5.3.2 የፌደራል መንግስት ካፒታል ወጪ

የፌዴራል መንግስት የካፒታል ወጪ የሚሸፈነው ከአገር ውስጥ ከመንግስት ግምጃ ቤት እና ከመ/ቤቶች የውስጥ ገቢ እንዲሁም ከውጪ ብድርና ዕርዳታ ነው፡፡ የ2016 በጀት ዓመት ከመንግስት የትኩረት አቅጣጫ አንጻር በመካሄድ ላይ ላሉ ነባር ፕሮጀክቶች አሁን ያለውን ዕቅድ ለማሳካትና እንዲጠናቀቁ ለማድረግ እና በግጭቱ ምክንያት የወደሙ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞው ይዞታቸው ለመመለስ ለመልሶ ማቋቋም ቅድሚያ በመስጠት በአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ መሰረት የዘላቂ ልማትን፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት ማስፋፋት፣ የግብርና ምርታማነት፣ የመስኖ ልማት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ግቦችን ለማሳካት እንዲያስችሉ ለተጀመሩ ፕሮጀክቶች

ማስፈጸሚያ እንዲጣጣም ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡በመሆኑም ለ2016 የፌደራል መንግስት የካፒታል ወጪ ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 146.1 ቢሊዮን፤ ከውጭ እርዳታ ብር 31.6 ቢሊዮን እና ከውጪ ብድር 25.7 ቢሊዩን በድምሩ 203.44 ቢሊዮን እንደሚሆን ታቅዷል፡፡ ይህም በ2015 በጀት ዓመት ከተፈቀደው ብር 218.1 ቢሊዮን አንጻር በብር 14.67 ቢሊዮን ወይም በ6.73 በመቶ ቅናሽ እንዳለው ያሳያል፡፡

## 5.3.3 የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ

የክልል መንግስታት የበጀት ድጋፍ የክልላዊ መንግስታት አብዛኛው ወጪ የሚሸፈነው ከፌዴራል መንግስት በሚተላለፍ የበጀት ድጋፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም መንግስት በክልሎች ለሚከናወኑት የገጠር መሰረተ ልማት፣ የአቅም ግንባታ እንዲሁም ድህነት ተኮር የወጪ ዘርፎች ትኩረት የሰጠ ነው፡፡ ለ2016 በጀት ዓመት ለክልልላዊ መንግስታት 214.07 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከመንግስት ግምጃ ቤት የተመደበው ብር 205.04 ቢሊዮን ሆኗል፡፡ በመሆኑም የ2016 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተደገፈው የበጀት ድጋፍ ከ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው አንጻር ምንም ዓይነት ጭማሪ የለውም፡፡ የ2016 በጀት ዓመት ጠቅላላ የክልሎች ድጋፍ ከሁሉም የፋይናንስ ምንጭ ለ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው ብር 209.38 ቢሊዮን ጋር ሲታይ በብር 4.69 ቢሊዮን ወይም በ2.2 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡

## 5.3.4 የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ

የዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ የዘላቂ የልማት ግቦችን ማሳካት እንዲቻል በክልሎች ለሚካሄዱ ዘላቂ ልማትና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ እና ለስራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም በክልሎች ለሚካሄዱ ለአነስተኛ እና መካከለኛ መስኖ ልማት የካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 14.0 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡ ከዚህ በላይ ቀጥሎ የበጀት ዝግጅቱ ታሳቢዎችና ማብራሪያዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

# 6. የ2016 ፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና ድጋፍ

የፌዴራል መንግሥት የ2016 በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት የአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ አካል የሆነውን የ2016 - 2018 የልማትና ኢንቨስትመንት እቅድ የተቀመጡ ግቦችን ከማስፈጸም አኳያ፣ የሀገር ደህንነት ከማስጠበቅ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጐችን ከመርዳት እና በጦርነቱ የወደሙ መሰረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች መልሶ ከማቋቋም እንዲሁም በቀጣይ ሊኖር የሚችለውን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎችና ዓላማዎች እና የ2016-2020 የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፍን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የአምስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት (2016-2018) በጀት ዝግጅት የ2015 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም መነሻ በማድረግ በፕሮግራሙ ዘመኑ መጨረሻ የታቀዱትን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት በመንግስት የተቀመጡ ግቦችን ከማሳካት አንፃር፣ ከመንግሥት የፋይናንስ አቅም፣ መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ተልዕኮና ማንዴት አኳያ ለውጤቶች፣ ለዋና ዋና ተግባራትና ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ወጪ በመገምገም በጀቱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ለፕሮግራም በጀት ዝግጅት እንዲረዳ አመልካች የበጀት ጣሪያ ከዝርዝር መመሪያ ጋር እንዲደርሳቸው ተደርጓል። በበጀት ጥሪው መሠረት አስፈጻሚ መ/ቤቶች የበጀት ጥያቄቸውን አቅርበው ከስራ ፀባያቸው አኳያ ከመ/ቤቶች ጋር የበጀት ስሚ ተከናውኗል፡፡

## 6.1. የ2016 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ዋና ዋና ታሳቢዎች

### 6.1.1. ጠቅላላ ታሳቢዎች

የፕሮግራም በጀት በጀትን ከውጤት ጋር የሚያዛምድ የበጀት አሰራር ስርዓት ሲሆን፣ ውጤትን ለመለካት፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ እቅድን ከበጀት ጋር ለማስተሳሰር እና የመደበኛና የካፒታል ወጪዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ ለ2016 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ታሳቢ የተደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ለ2016 በጀት ዓመት የተዘጋጀው በጀት የአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ አካል የሆነውን የ2016-2018 የልማትና ኢንቨስትመንት እቅድ እና

የፕሮግራም በጀት በማጣጣም የተቀመጡ ግቦችና አቅጣጫዎችን ከማስፈጸም አኳያ እና ሊኖር የሚችለውን የሀብት መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

- በዕቅዱ ዘመን ለማህበራዊና ለኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ ለኢንዱስትሪ ልማትና ለኤክስፖርት መስፋፋት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ፣ ለመስኖ ልማት እና ለግብርና ልማት የተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት በቀጣይም ትኩረት እንደሚሰጠው ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

- አዲሱ አደረጃጀት ከ2016 በጀት ዓመት ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚደረግና የመንግስት በጀት በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ ለመ/ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን የደመወዝና የስራ ማስኬጃ በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- በካፒታል ወጪ በመካሄድ ላይ ላሉ ነባር ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት እና በውጭ ፋይናንስ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ደግሞ የመንግስት ድርሻን ታሳቢ በማድረግ፣

- የሀገር ደህንነት ለማስጠበቅ ፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት ለተጐዱ ዜጐች የእለት እርዳታ ለማቅረብ እና ለልማታዊ ሴፍቲኔት የሚያስፈልገውን ወጪ ታሳቢ በማድረግ፣

- በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ መሰረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ለመመለስ የመልሶ ማቋቋም ስራን ታሳቢ በማድረግ፣

- ሊኖር የሚችለውን የአገር ውስጥ ብድር ጫና ግምት ውስጥ በማስገባት ለአገር ውስጥ እዳ ክፍያ እንዲሁም የውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በክልሎች በተጓዳኝ ፋይናንስ /Matching Fund/ ጭምር ለሚካሄዱ አነስተኛ እና መካከለኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች እና ለነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት፣

- መ/ቤቶች በተመደበላቸው በጀት የሚያከናውኑት የመሰረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ለህብረተሰቡ የሚያስገኙት ውጤቶችና ለውጦችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- የመንግስት መ/ቤቶች የቀረጿቸው ፕሮግራሞች ከየመ/ቤቱ ተልዕኮና ማንዴት ጋር የተጣጣሙ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ፤

- መ/ቤቶች ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጧቸውን አላማዎች እና ፕሮግራሞች በቅደም ተከተል እንዳቀረቡ ታሳቢ በማድረግ፤

- የፕሮግራም በጀት በቁጠባ፣ በብቃትና በውጤታማነት እንደሚመራና እንደሚተገበር ታሳቢ በማድረግ፣

የአምስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት /2016-2018/ የፕሮግራም በጀት መ/ቤቶች ካስቀመጡት ስትራቴጂክ ዓላማ፣ ግቦች፣ ከሚጠበቁ ውጤቶች እና ከ2015 የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም አኳያ በመገምገም የ2016 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ተዘጋጅቷል፡፡

## 6.1.2. የመደበኛ ወጪ ታሳቢዎች

- በየመ/ቤቱ እየተካሄደ ያለውን አዲሱን አደረጃጀት ታሳቢ ያደረገ እና የመንግስት በጀት በቁጠባና በውጤታማነት ላይ ያተኮረ እንዲሁም ለብክነት የተጋለጡ ወጪዎችን በአግባቡ ተፈትሸው የቀረቡ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

- ለነባርም ሆነ አዲስ መ/ቤቶች በሚያዝያ ወር የደመወዝ ፔሮል መሰረት የደመወዝ በጀት በመያዝና አዲስ ቅጥር እንደማይኖር ታሳቢ በማድረግ፣

- ከልማታዊ ሴፍቲኔት ውጪ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግሮች ለዜጎች የዕለት ዕለት ደራሽ ዕርዳታ ለማቅረብ የሚያስፈልገውን በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ በመደበኛ በጀት የሚያስከትለውን የወጪ ግምት ታሳቢ በማድረግ፣

- በአለም ገበያ የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ የተፈጠረውን የዋጋ ልዩነት ለመሸፈን የድጎማ በጀትን ታሳቢ በማድረግ ፣

- ከመ/ቤቶች የሚጠበቀው ውጤት እና ከሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት አኳያ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የግብዓት ወጪዎች በማስላት፣

- የመ/ቤቶችን የበጀት አጠቃቀም፣ የዋጋ ንረት እንዲሁም በመንግስት ተመን የወጣላቸውን /ምግብ፣ የውሎ አበል፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ወዘተ…/ መሰረት በማድረግ፣

- ከመንግስት ግምጃ ቤት ለሚገዙ መሳሪያዎች፣ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የቀረጥ ሂሳብ በእያንዳንዱ መ/ቤት እንዲያዝ በማድረግ፣

## 6.1.3. የካፒታል ወጪ ታሳቢዎች

- ከመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ አንፃር በአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የዘላቂ ልማት ዘርፎች እና የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት ማስፋፋት፣ የግብርና ምርታማነትን፣ የመስኖ ልማት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ግቦችን ለማሳካት እንዲያስችሉ ለተጀመሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ቅድሚያ በመስጠት፣

- በውጭ ፋይናንስ ጭምር ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች የውጭ ፋይናንስ ፍሰት በእርግጠኝነት በበጀት ዓመቱ ሊፈስ የሚችለውን የገንዘብ መጠን በበጀት እንዲያዝ በማድረግ፣

- በውጭ ፋይናንስ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ከመንግስት የሚያስፈልገውን ተጓዳኝ ፋይናንስ (Matching Fund) እንዲያዝ በማድረግ፣

- ከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ ከአዲሱ የዩኒቨርሲቲ ሪፎርም አኳያ ለትምህርት ጥራት አጋዥ ለሆኑ ወርክሾፕ፣ ላብራቶሪ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን ለማደረጀት እና ያሉትን ነባር ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ፣
- በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ መሰረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ለመመለስ የመልሶ ማቋቋም ስራን ታሳቢ በማድረግ፣
- አስፈጻሚ መ/ቤቶች ለፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጡና ፕሮጀክቶች በታቀደው ወጪ፣ ጊዜና ጥራት እንዲካሄዱ በማድረግ የሀብት ብክነት እንደማይኖር ግምት ውስጥ በማስገባት፣
- ለተወሰኑ የመንግስት መ/ቤቶች ምቹ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር እንዲቻል በጥናት ላይ የተመሰረተ ለቢሮ ህንጻ ጥገናና እድሳት በጀት ታሳቢ በማድረግ፣
- በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የመ/ቤቶች የቢሮ ኪራይ ወጪ ለመቀነስ እና ምቹ የሥራ ሁኔታን ለማመቻቸት በ2016 በጀት ዓመትም የመንግስት ቢሮዎች ግንባታ በማዕከል በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እንደሚካሄድ ታሳቢ ተደርጎ በጀቱ ተደግፏል፡፡

በአጠቃላይ የ2016 በጀት አመት የበጀት ዝግጅት ከፍ ብለው የተመለከቱትን ታሳቢዎችና አቅጣጫዎች ግምት ውስጥ ያስገባና ያስቀመጠ ሲሆን ከመንግሥት የሚመደበው የበጀት ድጋፍም በመደበኛና በካፒታል ወጪዎች በመለየት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 6.2. ጠቅላላ በጀት

ለ2015 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 345.12 ቢሊዮን ፣ ለካፒታል ወጪ ብር 218.11 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 209.38 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14.00 ቢሊዮን በአጠቃላይ ብር 786.61 ቢሊዮን መፈቀዱ ይታወሳል፡፡

ለ2016 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 370.14 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 203.44 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 214.07 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14.0 ቢሊዮን በጠቅላላው 801.65 ቢሊዮን ብር ተደግፏል፡፡ በዚህም


መሠረት የፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ የ2016 በጀት ለ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት በብር 15.04 ቢሊዮን ወይም የ 1.91 በመቶ ዕድገት ያሳያል።

## የ2016 በጀት ዓመት የበጀት ድጋፍ

በቢሊዮን

| የወጪ አይነት | የ2015 የጸደቀ በጀት | የ2016 የተደገፈ በጀት | ልዩነት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በመጠን | በ% |
| 1 | 2 | 3 | 4=3-2 | 5=4/2 |
| መደበኛ | 345.12 | 370.14 | 25.02 | 7.25 |
| ካፒታል | 218.11 | 203.44 | -14.67 | -6.73 |
| ክልል ድጋፍ | 209.38 | 214.07 | 4.69 | 2.24 |
| የዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ (SDGs) | 14.00 | 14.00 | 0.00 | 0.00 |
| ድምር | 786.61 | 801.65 | 15.04 | 1.91 |

ከሠንጠረዡ ላይ መረዳት እንደሚቻለው ለ2016 ከተደገፈው በጀት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ የሚገኘው ለመደበኛ ወጪ የተመደበው የበጀት ድጋፍ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ የተደገፈው ደግሞ ለክልል ድጋፍ ነው፡፡




የበጀት ድጋፉና ድልድሉ በዋና ዋና ወጪዎች ይህን ሲመስል፣ ለመደበኛና ለካፒታል ወጪዎች የተመደበውን በጀት በዘርፍ በመለየት ከዚህ በታች በአጭሩ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

### 6.2.1 የመደበኛ ወጪ


የ2016 በጀት ዓመት የመደበኛ ወጪ ብር 370.14 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ብር 80.61 ቢሊዮን (21.78%)፣ ለኢኮኖሚ አገልግሎት ብር 6.9 ቢሊዮን (1.86%)፣ ለማኅበራዊ አገልግሎት ብር 54.24 ቢሊዮን (14.65%) እና ለሌሎች ክፍያዎች ብር 228.39 ቢሊዮን (61.70%) ነው፡፡ ከሌሎች ክፍያ ውስጥ ደግሞ ለዕዳ ክፍያ ብር 159.2 ቢሊዮን (69.7%) እና ለመጠባበቂያ ብር 47.33 ቢሊዮን (20.7%) የተመደበ ነው፡፡

በአጠቃላይ የ2016 በጀት ዓመት መደበኛ ወጪ በ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 345.12 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር በብር 25.02 ቢሊዮን ወይም የ 7.25 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

## የ2016 በጀት ዓመት መደበኛ ወጪ

በቢሊዮን ብር

| አገልግሎት | የ2015 የጸደቀ በጀት | የ2016 በጀት | | ልዩነት | | ድርሻ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተጠየቀ | የተደገፊ | በመጠን | በ% | |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5=4-2 | 6=5/2 | |
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 111.69 | 112.70 | 80.61 | -31.08 | -27.83 | 21.78 |
| ኢኮኖሚ | 7.00 | 11.20 | 6.90 | -0.10 | -1.43 | 1.86 |
| ማህበራዊ | 53.76 | 71.60 | 54.24 | 0.48 | 0.89 | 14.65 |
| ሌሎች | 172.67 | 232.04 | 228.39 | 55.72 | 32.27 | 61.70 |
| የበጀት ድጋፍ | 22.63 | 21.80 | 21.86 | -0.77 | -3.40 | |
| ዕዳ ክፍያ | 125.96 | 159.20 | 159.20 | 33.24 | 26.39 | |
| መጠባበቂያ | 24.09 | 51.00 | 47.33 | 23.24 | 96.47 | |
| ድምር | 345.12 | 427.54 | 370.14 | 25.02 | 7.25 | |




### 6.2.1.1 አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ

በ2016 በጀት ዓመት የተደገፈው በጀት ብር 80.61 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 111.69 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 31.08 ቢሊዮን ወይም 27.83 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የሀገር መከላከያ በጀት ቅናሽ በማሳየቱ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን፣ ለገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ለኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ለጉምሩክ ኮሚሽን፣ ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን እና ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 6.2.1.2 ኢኮኖሚ ዘርፍ

በኢኮኖሚ ዘርፍ በ2016 በጀት ዓመት የተደገፈው መደበኛ ወጪ ብር 6.90 ቢሊዮን ሲሆን ለ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 7.00 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 0.1 ቢሊዮን ወይም በ 1.43 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን፣ ለማሪታይም ባለሥልጣን፣ ለግብርና ሚኒስቴር፣ ለነዳጅና ኤነርጂ ባለስልጣን፣ ለግብርና ባለሥልጣን፣ ለኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት እና ለቡናና ሻይ ባለሥልጣን ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 6.2.1.3 ማኅበራዊ ዘርፍ

ለማኅበራዊ ዘርፍ ለ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 54.24 ቢሊዮን ሲሆን፣ ለ2015 በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት ብር 53.76 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 0.48 ቢሊዮን ወይም የ 0.89 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ለጭማሪው ዋናው ምክንያት ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት፣ ለአክሱም፣ ለአዲስ አበባ፣ ለደብረብርሃን፣ ለቡሌ ሆራ እና አምቦ ዩኒቨርሲቲ ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ በመደረጉ ነው።

### 6.2.1.4. ሌሎች

ለሌሎች አገልግሎቶች ለ2016 በጀት ዓመት ብር 228.39 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን ለዕዳ ክፍያ 69.7 በመቶ ፣ ለመጠባበቂያ በጀት 20.7 በመቶ እና ለበጀት ድጋፍ 9.6 በመቶ እንዲሆን የተደገፈ ነው። በመሆኑም ብር 159.20 ቢሊዮን ለዕዳ ክፍያ፣ ብር 47.33 ቢሊዮን ለመጠባበቂያ እንዲሁም ብር 21.86 ቢሊዮን ለበጀት ድጋፍ የተደገፈ ነው።


### 6.2.1.5 መደበኛ ወጪ በኢኮኖሚ ጠቀሜታ

የ2016 በጀት ዓመት ጠቅላላ የመደበኛ ወጪ በኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሲታይ ብር 67.45 ቢሊዮን ወይም 18.2 በመቶ ለደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ብር 302.68 ቢሊዮን ወይም 81.8 በመቶ ለስራ ማስኬጃ የተደገፈ ነው። ለ2016 በጀት ዓመት ለደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች የተደገፈው ለ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው ብር 75.58 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር የብር 8.13 ቢሊዮን ወይም የ10.76 በመቶ ቅናሽ አለው። በሌላ በኩል የ2016 የሥራ ማስኬጃ ወጪ ለ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ብር 269.54 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 33.14 ቢሊዮን ወይም የ12.3 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

# የ2016 እና የ2015 የመደበኛ ወጪ የደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና የሥራ ማስኬጃ በጀት ንጽጽር

በቢሊዮን ብር

| አገልግሎት | የ2016 በጀት አመት | | | የ2015 የጸደቀ በጀት | | | ልዩነት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች | | ሥራ ማስኬጃ | |
| | ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች | ሥራ ማስኬጃ | ድምር | ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች | ሥራ ማስኬጃ | ድምር | መጠን | % | መጠን | % |
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 33.10 | 47.51 | 80.61 | 42.27 | 69.42 | 111.69 | -9.17 | -21.69 | -21.91 | -31.56 |
| ኢኮኖሚ | 2.75 | 4.14 | 6.90 | 2.80 | 4.20 | 7.00 | -0.05 | -1.79 | -0.06 | -1.43 |
| ማህበራዊ | 22.60 | 31.64 | 54.24 | 20.63 | 33.13 | 53.76 | 1.97 | 9.55 | -1.49 | -4.50 |
| ሌሎች | 9.00 | 219.39 | 228.39 | 9.88 | 162.79 | 172.67 | -0.88 | -8.91 | 56.60 | 34.77 |
| ድምር | 67.45 | 302.68 | 370.14 | 75.58 | 269.54 | 345.12 | -8.13 | -10.76 | 33.14 | 12.30 |




## 6.2.2 የካፒታል ወጪ

የ2016 በጀት ዓመት ጠቅላላ የካፒታል ወጪ ብር 203.44 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 146.13 ቢሊዮን ከአገር ውስጥ ምንጭ፣ ብር 31.61 ቢሊዮን ከውጭ እርዳታ እና ብር 25.7 ቢሊዮን ከውጭ ብድር የሚሸፈን ነው፡፡ ጠቅላላ ለካፒታል የተያዘው በጀት ለ2015 በጀት ዓመት ከጸደቀው በጀት ከብር 218.11 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 14.67 ቢሊዮን ወይም 6.73 በመቶ ቅናሽ ያሳያል፡፡


የ2016 በጀት ዓመት የካፒታል ወጪ ከ2015 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር ለአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ ብር 1.76 ቢሊዮን ጭማሪ በማድረግ እንዲሁም ከኢኮኖሚ ዘርፍ ብር 3.97 ቢሊዮን፣ ከማህበራዊ ዘርፍ ብር 11.45 ቢሊዮን እና ለሌሎች ዘርፍ ብር 1.01 ቢሊዮን ቅናሽ በማድረግ ተደግፏል፡፡ የ2016 የካፒታል ወጪ ከ2015 በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር ለግብርና ሚኒስቴር፣ ለውሃና ኤነርጂ

ሚኒስቴር፣ ለጤና ሚኒስቴር እና ለኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር እንዲሁም ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የበጀት ድጋፍ ጭማሪ ተደርጓል።

## የ2016 በጀት ዓመት የካፒታል ወጪ

በቢሊዮን ብር

| አገልግሎት | የ2015 የጸደቀ በጀት | የ2016 በጀት | | ልዩነት | | ድርሻ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተጠየቀ | የተደገፈ | በመጠን | በ% | |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5=4-2 | 6=5/2 | |
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 29.65 | 36.82 | 31.41 | 1.76 | 5.94 | 15.44 |
| ኢኮኖሚ | 133.26 | 146.93 | 129.29 | -3.97 | -2.98 | 63.55 |
| ማህበራዊ | 48.69 | 58.31 | 37.24 | -11.45 | -23.52 | 18.31 |
| ሌሎች | 6.51 | 7.16 | 5.50 | -1.01 | -15.51 | 2.70 |
| ድምር | 218.11 | 249.22 | 203.44 | -14.67 | -6.73 | 100.00 |




### 6.2.2.1 ከካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው

የ2016 በጀት አመት የካፒታል ወጪው ሲዘጋጅና ድጋፍ ሲሰጥ ዘላቂ ልማት የማምጣት፣ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን የማረጋገጥ እና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከካፒታል ወጪው ውስጥ ከፍተኛ ትኩረትና የበጀት መጠን ያላቸው የሥራ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በመሠረተ ልማት በኩል የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ለዋና መንገዶች፣ ለአገናኝ መንገዶች ግንባታ እና ነባሮቹን ለማጠናከርና ለማሻሻል ለተጀመሩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 60.0 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡ በአጠቃላይ ለመንገድ ፕሮጀክቶች የውጭ ፋይናንስን ጨምሮ ብር 67.6 ቢሊዮን የተደገፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለዋና መንገዶች ማጠናከርና ማሻሻል ብር 16.1

ቢሊዮን ለአገናኝ መንገዶች ግንባታና ማሻሻያ ብር 44.4 ቢሊዮን እና ለመንገዶች ከባድ ጥገና ብር 3.0 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል።

- ለከፍተኛ ትምህርት ነባር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብር 17.0 ቢሊዮን እና ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 100.0 ሚሊዮን እንዲሁም ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፖኬጅ የውጭ ፋይናንስ ጨምሮ ብር 660.6 ሚሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ለነባርና ለትላልቅ መስኖዎች ግንባታ ብር 6.1 ቢሊዮን እንዲሁም በቆላማ አካባቢዎች የቴክኖሎጂ ስርፀት በማድረግ የአካባቢውን ህብረተሰቡ ኑሮ ለማሻሻል 1.5 ቢሊዮን በካፒታል በጀት ተደግፎ ቀርቧል፡፡ ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ የመካከለኛና የትናንሽ መስኖዎች ግንባታ በቀጥታ በክልሎች በኩል ለመተግበር በዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ ስር ብር 8.00 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ ንብረቶች እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ለማድረግ ለመልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 20.0 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡


- የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽንን በተመለከተ ብር 8.23 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 2.26 ቢሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎችን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ለሟሟላት የተደገፈ ነው፡፡

- የግብርናውን ዘርፍ በመስኖ ልማት ለመደገፍ በአነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ለሚካሄድ የተቀናጀ አነስተኛ የመስኖ ልማት ኘሮጀክት በልዩ ሁኔታ ብር 600.0 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- በገጠር የስራ ዕድልና የምግብ ዋስትና ጋር ለተገናኘው ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 7.3 ቢሊዮን እና ከውጭ ፋይናንስ ብር 5.0 ቢሊዮን በድምሩ ብር 12.3 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡ በተመሳሳይ ለከተማ ምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት እና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 3.3 ቢሊዮን እና ከውጭ ፋይናንስ ብር 6.8 ቢሊዮን በድምሩ ብር 10.1 ቢሊዮን ተደግፏል፡፡

- ለጤና ሴክተር ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 4.2 ቢሊዮን እና ከውጭ ፋይናንስ ብር 12.6 ቢሊዮን በድምሩ ብር 16.8 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡
- የመንግስት አገልግሎቶችን በተመቻቸ ቦታ ለመስጠትና የቢሮ ኪራይ ለመቀነስ እንዲቻል ለመንግሥት ቢሮዎች ግንባታ ፕሮጀክት ብር 1.6 ቢሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ተደግፎ ቀርቧል፡፡

ከዚህ በላይ የተሰጡት ማብራሪያዎች በዋና ዋና ወጪዎች ላይ ያተኮሩ ሲሆን በአስፈጻሚ መ/ቤቶችና በበጀት ዓይነት በመለየት በጥራዝ ሁለት የበጀት ሠነድ ውስጥ በዝርዝር መግለጫ ተሰጥቶበታል፡፡



### 6.2.3. ከፌዴራል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው

ከዚህ በላይ በፌዴራል የመደበኛና የካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የመደበኛና የካፒታል ወጪ ተዳምረው ሲታይ የክፍላተ ኢኮኖሚ ድርሻ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ከአጠቃላይ ከፌዴራል በጀቱ ከብር 573.58 ቢሊዮን ውስጥ 34.5 በመቶ ድርሻ ያላቸው መንገድ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ውሀና ኤነርጂ፣ ግብርና እና የከተማ ልማት ናቸው፡፡ ይህም ከ2015 በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር የበጀት ድርሻው የቀነሰው የዕዳ ክፍያ እና የማዳበሪያ ድጐማ በጀት በመጨመሩ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ድጋፍ በጀት በመያዙ ነው፡፡ በፌዴራል ደረጃ የግብርና፣ የጤና እና የውሃ ሴክተር በጀት ድርሻ ከሌሎች አነስተኛ ሆኖ ቢታይም በአብዛኛው ስራዎቹ በክልሎች የሚካሄዱ በመሆኑ የእነዚህ ሴክተሮች የበጀት ድርሻ የክልሎችን ሲጨምር በሀገር ደረጃ ከፍተኛ እንደሚሆን ይገመታል፡፡

በተጨማሪም የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንና ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ትርጉም ላላቸው የማኑፋክቸሪንግ፣ ኤክስፖርትና የከተማ ልማት ዘርፎች ከፍ ያለ በጀት መመደቡን ከሠንጠረዡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዕዳ ክፍያ ደግሞ 27.76 በመቶ እንዲሁም መንገድ 11.93 በመቶ ከአጠቃላይ ከፌዴራል በጀቱ ውስጥ ድርሻ አላቸው፡፡

## ከፌዴራል የመደበኛና የካፒታል ወጪ ውስጥ

## ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው

በቢሊዮን ብር

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ወጪዎች | መጠን | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ዕዳ ክፍያ | 159.2 | 27.76 |
| 2 | መንገድ | 68.4 | 11.93 |
| 3 | ትምህርት | 55.77 | 9.72 |
| 4 | መከላከያ | 50 | 8.72 |
| 5 | ጤና | 22.57 | 3.93 |
| 6 | ውሀ ሀብትና ኤነርጂ | 19.51 | 3.4 |
| 7 | ግብርና | 19.21 | 3.35 |
| 8 | ፍትህና ደሕንነት | 17.95 | 3.13 |
| 9 | የከተማና ልማት | 12.37 | 2.16 |
| 10 | ትራንስፖርት እና መገናኛ | 9.58 | 1.67 |
| 11 | አደጋ መከላከል | 8.72 | 1.52 |
| 12 | ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም | 3.98 | 0.69 |
| 13 | ባህልና ስፖርት | 2.71 | 0.47 |
| 14 | ሌሎች | 123.61 | 21.55 |
| | ድምር | 573.58 | 100.00 |

## 7. የወጪ አሸፋፈን


በ2016 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ከሀገር ውስጥ የገቢ ምንጮች እና ከውጭ ዕርዳታ በድምሩ ብር 520.60 ቢሊዮን እንደሚሰበሰብ ተገምቷል፡፡ ከዚሁ ውስጥ ከአገር ውስጥ ገቢ ብር 479.49 ቢሊዮን፣ በቀጥታ በጀት ድጋፍ ከሚገኝ ከመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ዕርዳታ ብር 6.34 ቢሊዮን እና ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ ብር 34.77 ቢሊዮን ሊገኝ እንደሚችል ታቅዷል፡፡

በሌላ በኩል ለፌዴራል መንግሥት የመደበኛ ወጪ 370.14 ቢሊዮን (46.17%)፣ የካፒታል ወጪ ብር 203.44 ቢሊዮን (25.38%)፣ ለክልሎች ድጋፍ ብር 214.07 ቢሊዮን (26.7%) እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 14.0 ቢሊዮን (1.75%) በድምሩ ብር 801.65 ቢሊዮን ወጪ ታቅዷል፡፡ በዚህም መሠረት በገቢው 520.60 ብር ቢሊዮን እና በጠቅላላ ወጪው ብር 801.65 ቢሊዮን መካከል የብር 281.05 ቢሊዮን የበጀት ጉድለት ይታያል፡፡

ይህም የበጀት ጉድለት ማለትም ብር 281.05 ቢሊዮን በቀጥታ በጀት ድጋፍ ከሚገኝ ከመሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ብድር ብር 7.44 ቢሊዮን፣ ከፕሮጀክት ብድር ብር 31.57 ቢሊዮን እና ከሀገር ውስጥ ብድር ብር 242.04 ቢሊዮን ለመሸፈን ታቅዷል፡፡ ከጠቅላለ የበጀት ጉድለት ውስጥ ብር 53.7 ቢሊዮን ለመንግስት ዋና እዳ ክፍያ የሚውል ነው፡፡ በመሆኑም የተጣራ የበጀት ጉድለት ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ያለው ድርሻ 2.1% ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሀገር ውስጥ ብድር ድርሻ 2.2% በመሆኑ የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ተግባራዊ ከሚደረገው የገንዘብ ፖሊሲ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ በመሆኑ በዋጋ ንረት ላይ ተጽእኖ እንደማያሳድር ይታመናል፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥና ሥዕላዊ መግለጫ ተመልክቷል፡፡

# የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የገቢና ወጪ ዕቅድ ማጠቃለያ (በቢሊዮን ብር)

| | | |
|---|---|---|
| **I. ጠቅላላ ገቢ** | | **520.60** |
| 1.1 ታክስ ገቢ | 440.83 | |
| 1.2 ታክስ ያልሆኑ | 38.66 | |
| 1.3 መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ዕርዳታ | 6.34 | |
| 1.4 ፕሮጀክት ዕርዳታ | 34.77 | |
| **II. ጠቅላላ ወጪ** | | **801.65** |
| 2.1. መደበኛ ወጪ | 370.14 | |
| 2.2. ካፒታል ወጪ | 203.44 | |
| 2.3 የክልሎች ድጋፍ | 214.07 | |
| 2.4. ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ | 14.00 | |
| **III. የበጀት ጉድለት (I – II)** | | **-281.05** |
| **የውጭ ሀገር ብድር** | | **39.01** |
| 3.1 መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ብድር | 7.44 | |
| 3.2. ፕሮጀክት ብድር | 31.57 | |
| **የሀገር ውስጥ ብድር** | | **242.04** |
| 3.3. የሀገር ውስጥ ብድር | 242.04 | |


የ 2016 በጀት አመት የፌዴራል መንግስት ገቢ፣ የውጭ ዕርዳታና ብድር
/በቢሊዮን ብር/
የአገር ውስጥ ገቢ, 479.48, 59.8%
መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ድጋፍ 6.35, 0.8%
መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ብድር 7.44, 0.9 %,
ፕሮጀክት ብድር 31.57, 3.9 %,
ፕሮጀክት ዕርዳታ ,34.77, 4.3 %,
የሀገር ውስጥ ብድር, 242.04, 30.2 %,